ወገኖቼ እስራኤል ዘሥጋን የ ሚጠብቃቸው ንጉሥ ባንቺ ይ ነግሣልና። ታሪክ ነቢዩ ሚክያ ስ ነው ሌላውን ሲያስተምር ውሉ ወደ ግታ በቤተ ልሔ ም በሁል አልፎ ሲሄድ ተፈ ታ ምድረ በዳ ሆና ቋያ በቅ ሎባት አየ። እንዲህ እንጂ እ ንደሆንሽ አትቀሪም ንጉሥ ይ ነግሥብሽል የነጋሪት ድምፅ ይ ሰማብሽል ድንኳን ይተከልብሽ ል እስራኤል ደጅ ይጠኑብሽ ል አሕዛብ ይገብሩብሽል ብሎ ትንቢት ተናግሯል ይህም አ ልቀረ ዘሩባቤል ነግሦባታል እ ስራኤል ደጅ ጠንተውባታል የነጋሪት ድምፅ ተሰምቶባታል አሕዛብ ገብረውባታል ድንኳን ተተክሎባታል፤ ይህም ወገኖቼ እ ስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቃቸ ው ንጉሥ ከርስቶስ ባንች ይ ወለዳልና ።ዘሩባቤል እንደ ነገ ሠ ጌታ ተመልዶባታል። ድንኳ ን እንደ ተተከለበት የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል ።ነጋሪት እንደ ተሰማበት ቅዳሴ መላእ ክት ተሰምቶባታል። እስራኤል ደጅ እንደ ጠኑ መቶው ነገደ መላእክት ደጅ ጠንተውባታል አሕዛብ እንደ ገበሩ ሰብአ ሰ ገል ገብረዋል።እንድም አንቺ የኤፍራታ ልጅ እመቤታችን በይሁዳ ከነገሡ ነገሥታት ብ ትበልጭ እንጂ አታንሽም።ወ ገኖቼ እስራኤል ዘነፍስን የሚ ጠብቃቸው ንጉሥ ክርስቶስ ባ ንቺ ባሕርይ ይወለዳል፤ እምኔ ኪ ካንች ይወለዳልና።

፯ ወእምዝ ጸውዖ ሄሮድስ ለ ሰብአ ሰገል ጽሚተ።

፯ ከዚህ በኋላ ሰብአ ሰገልን በቂ ይታ ጸራቸው ከሀናትን ጠይቆ ባጻራሽ አውጥቶ ሰብአ ሰ ገልን በእልፍኝ ጠራቸው፤ አሁን ከኛ ጠይቆ ይነግራ ቸዋል እንዳይሉት ።አንድም ከ ሀናትን በእልፍኝ አስወጥቶ ሰብአ ሰገልን በአጻራሽ አስጠ ራቸው። ይኸም ውዳሴ ከንቱ ሽቶ ነው።እኛስ እንኳ አውቀ ን ስንመጣ እሱ ከዚህ ሁኖ እ ስከ ዛሬ ሳይሰማ ኑሯል ይሉ ኛል ብሎ።

ወተጠየቀ እምኔሆሙ መዋዕ ሊሁ በዘአስተርአዮሙ ከዋክ። ከዋክብ የታየበትን ቀን ጠየ ቃቸው ። አንድም ከዋክቡ በ ታየበት ቀን የጌታን ዘመኑን አውቆ ተረዳው።ይህን ከዋክ ከያችሁ ምን ያህል ዘመን ሁ ኖታል አላቸው።ሁለት ዓመት ሁኖታል አሉት፤ ለካ ያም ብላ ቴና ሁለት ዓመት ሁኖታል አለ

፰ ወፈነዎሙ ኀበ ቤተ ልሔም ቤተ ልሔም ነው ብሎ ሰደዳ ቸው።

ወይቤሎሙ ሐዊረከሙ ተሰ አሉ ጥዩቀ በእንተ ውእቱ ሕፃን ወእምከመ ረከብክምዎ ግብኡ ኀቤየ ወዜንዉኒ።

ሂዳችሁ የብላቴናውን ነገር ጠ ይቃችሁ ድርሱን ያገኛችሁት እንደሆነ በኔ በኩል ተመል ሳችሁ ንገሩኝ አላቸው።

ከመ እምጸአ አነሂ ወእስግድ ሉ።

እኔም መጥቼ እሰግድለት ዘን ድ። ለሄሮድሳውያን ጉሕሉት ልማዶቸው ነውና እስግድ ሉቱ አለ እንጂ።እቅትሉ ሊል ነው ሐተታ እንዲህማ ከግለት ተ ቀድሞ ሄዶ አይነግራቸውምን ቢሉ ከሀናቱ ዘመዶቹ ናቸው ና ልከው ያሸኹብኛል ብሎ። በንድ ሂዶ አይገድለውም ነበር ቢሉ ሰብአ ሰገል ይገላግሉኛል ብሎ።አይሆንም ያልኋቸው እ ንደሆነ ዕልፍ ዕልፍ ሠራዊት አስከትለው መጥተዋል አግባ መልስ ብለው ይጸሉኛል ብሎ አንድም እኛ ብቻ መስሉን የሀ ገሩም ነገሥታት ያምኑበታልሳ ብለው የሰብአ ሰገል ሃይማኖ ታቸው እንዲጸናላቸው። መንፈ ስቅዱስ አፋን ከፍቶ ፊቱን ጸ ፍቶ እናገረው።

ወሰሚዖሙ ሖሩ እምኀበ ንጉ ሥ።

ቤተ ልሔም ነው ያላቸውን ሰ ምተው ወተአዚዘሙ ይላል፤ ወእምከመ ረከብክምዎ ግብኡ ኀቤየ ያላቸውን ሰምተው ን ጉሥ ነውና ይበጅ ያድርግ ብ ለው ሄዱ።

፱ ወናሁ ከከብ ዘርእዩ በምሥራ ቅ ይመርሆሙ እስከ ሶበ አብ ጽሐሙ ቤተ ልሔም፤

፱ በሥምራቅ ያዩት ከከብ ቤተ ልሔም እስኪያደርሳቸው ያመ ራቸው ነበር።

ወቆመ መልዕልተ በዓት ኀበ

ሀሎ ሕፃን ።
ባለበት ቦታ በሰው ቁመት ልክ ዘቅዝቆ ቆመ ። በጣት ጠቅሶ እንደ ማሳየት ።

፲ ወርእዮ·ሙ· ኮከበ ተፈሥሑ· ዓቢየ ፍሥሐ።

፲፩ ከከቡን አይተው ፈጽመው ደስ አላቸው·።ለልማዱ ከሰው· ሲያርሱ ያሰወራቸው· ከሰው· ሲለዩ ይመራቸው· ነበር አሁን ቢገለጽላቸው· እሱ እንጂ ቢሆን ነው· ብለው·።አንድም ስንኳን ሁለት ዓመት የሄዱለት ነገር ሁለት ሰዓት የሔዱለት ነገር ሲፈጸም ደስ ያሰኛልና ። አንድም እንዲህ መርቶ ከምን ያደርሰን ይሆን ። ከባሕር ያጠልቀን ከያዝ ያደርሰን ይሆን ብለው· ነበርና ከሰቡት ቢያደርሳቸው· ደስ አላቸው·።አንድም የሚቀድመው· አለ፡

፲፪ ወበቂያመ· ውስተ ቤት ረከብዎ ለሕፃን ምስለ ማርያም እመ· መዝ ፸፭ ፲

፲፫ ከቤት ገብተው· ብላቴናውን ከናቱ ጋራ· አይተው·።ከዚህ በኋላ ከከቡን አይተው· አምሳያው· ሁኖ ቢያገኙት ፈጽሞ ደስ አላቸው·።ቤት በዓት ጎል ይላል አብነት ።ቤት ቢል ዮሴፍ እንደ ዳስ አድርጎ ጥሶ· ነበርና ።በዓት ያለ እንደሆነ ኢዮስያስ በጨው· ማሸጋ ግምብ ዓሠርቶ ነበርና፤ጨውን ሲልሱ እንስሳት እየጋጡ አጕድጕደውት ነበርና ። ጎል ያለ እንደሆነ የተመቸ የእንስሳት ማደሪ ሁኖ ነበርና ።
ወወድቁ ወሰገዱ ሎቱ ።
ከፈረስ ከሰረገላ ወርደው· ሰገዱለት ። አንድም መላልሰው· ሰገዱለት ። ሐተታ ፡ እንደ ስናሩ ንጉሥ ጃን ተከል ሲደርስ ይሰግዳል ።የታዘዘ ብላቴና መጥቶ ተነሥ ብለው·ሃል ይለዋል ።ዳግም አልፎ ይሰግዳል ። ተነሥ ብለው·ሃል ይለዋል እንዲህ ኢያለ ከዚያ ሲደርስ እጅ ነሥቶ ከዙፋኑ በቀኝ አብሮ ይቀመጥ ነበር ።
ወአርኃዉ መዝግብቲሆ·ሙ·።ሣጥናቸውን ከፈቱ ።እየራሳቸው· ጭነዋል ያሉ እንደሆነ የተመቸው·።አንድ ነው ያሉ እንደሆነ ሰደፋ ብዙ ነውና፡እንደ ሰደፍ ነፍጥ ።አንድም ፈትሑ· ወአርኃዉ ይላል ሣጥናቸውን ከፈቱ ከረጅዎቸውን ፈቱ ።
ወአብኡ ሎቱ አምኃ ወርቀ ከርቤ ወስኒን።
ወርቁን ዕጣኑን ከርቤውን ግብር አገቡለት ። ሐተታ ወርቅ አመጡለት ይህን የምንገብራቸው· ነገሥታት ቀድሞም ፍጡራን ኋላም ኃላፍያን ናቸው· አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርህ ነህ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ ። ዕጣን አመጡለት ይህን የምናጥናቸው· ጣዖታት ቀድሞም ፍጡራን ኋላም ኃላፍያን ናቸው· ። አንተ ግን ቀድሞም ያልተፈጠርህ ኋላም የማታልፍ ነህ ሲሉ ። ከርቤ አመጡለት ምንም ቀድሞ ያልተፈጠርህ ኋላም ያማታልፍ ብትሆን በሰውነትህ መራራ ሞትን ጦቀበል አለብህ ሲሉ ። አንድም ወርቅ ጽሩይ ነው፤ ጽሩየ ባሕርይ ነህ ሲሉ ።ዕጣን ምውዝ ነው፤ምውዘ ባሕርይ ነህ ሲሉ ። ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል የተለየውን አንድ ያደርጋል ።አንተም ከግህበረ መላእክት የተለየ አዳምን አንድ ታደርገዋለህ ጽንዓ ነፍስ ሰጥተህ ታጸናዋለህ ሲሉ ። አንድም ወርቅ ጽሩይ ነው ባንተ ያመኑ ምዕመናን ጽሩያነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው· ሲሉ፤ዕጣን ምውዝ ነው፤በንተ ያመኑ ምዕመናን ምውዛነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው· ሲሉ ።ከርቤ አመጡለት በዕለተ ዓርብ ያቀምሱታልና ።አንድም ወርቅ የሰማዕታት ምሳሌ ነው· ከመ ወርቅ በእሳት ፈተኖመ· ለሰማዕት እንዲል ዕጣን የባሕታውያን ።ከሩቅ እንዲሸት ባሕታውያንም በተስፋ ይኖራሉ ።ከርቤ የምዕመናን በፍቅር አንድ ይሆናሉና ፤ወርቅ አመጡለት ወርቅ የሃይማኖት ምሳሌ ወርቅ ጽሩይነቱም ግብዝነቱም የሚታወቅ በእሳት ሲፈተን ነው ።የሃይማኖትም ጽሩይነቱና ግብዝነቱ የሚታወቅ መከራ ሲቀበሉበት ነውና ።ዕጣን የተስፋ ፤ዕጣን ከሩቅ እንዲሸት ።ተስፋም ያልያዙትን እንደያዙት ያላዩትን እንዳዩት ታደርጋለችና ። አሚንሰ ትሬሰዮ ለዘኢሀለወ ከመ ዘሀለወ እንዲል ። ከርቤ የፍቅር ያ አንድ እንዲያደርግ ፍቅርም አንድ ታደርጋለችና ።ሃይማኖት ፍቅር ተስፋ ገንዘቦችህ ናቸው· ሲሉ ። ወርቅ ዕጣን ከርቤ ገበሩለት ።አንድም ወርቅ የመላእክት

ዕጣን የደቂቀ አዳም ከርቤ የ
ከልዕ ፍጥረት። ከመ ለስሙ ለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ይስግዱ ኵ
ሉ ብርክ ዘውስተ ሰማይ ወዘ
ውስተ ምድር ወዘታሕተ ምድ
ር እንዲል። መላእክት ደቂቀ አ
ዳም ከልዕ ፍጥረት ገንዘቦችህ
ናቸው ሲሉ ወርቅ ዕጣን ከርቤ
አመጡለት። ይህስ ከወዴት የ
መጣ ነው ቢሉ ሶስቱ መላእ
ክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ
ገብርኤል ቅዱስ ሩፋኤል ወ
ርቅ ዕጣን ከርቤ አምጥተው
ለአዳም ሰጡት። አዳም ንሥኢ
ኅጼኪ ብሎ ለሔዋን ሰጣት
ሔዋን ለሴት ሰጠችው ከሴት
ሲወርድ ሲዋረድ ከኖኅ ደርሱ
አል። ኖኅ ከመርከብ ሲገባ ይዘ
ት ገብታል ሲወጣም ይዘት ወ
ጥታል በሚሞትበት ጊዜ ሴምን
ልጁን ከወንድምህ ከካም ወገ
ን ደግ ልጅ ይወለዳልና ካባ
ት ከናቱ አሰናብተህ ወርቁን
ዕጣኑን ከርቤውን አጽመ አ
በውን አስጠብቀው ሥራት
ሥራበት ብሎታል። ካባት ከና
ቱ አሰናብቶ ወርቁን ዕጣኑን
ከርቤውን አሸክሞ ሲሄድ ወ
ንድሞቹ ያፈትና ከም ተከተ
ሉት እናንተ አልታዘዛችሁም
የታዘዝን እኛ ነን ተመለሱ
አላቸው ተመለሱ ፣ መልአክ
ተገልጾ እየመራቸው ሄዱ ዱ
ዳሌም ሲደርሱ ጕድጓዳ በታ
አገኙ ዓጽመ አበውን ቀብሮ
ሶስቱን ንዋያት ሰጥቶ ሥራት
ይሠራበታል ከሴት አትድረስ
ዳባ ልበስ ሥጋ አትብላ ጠጅ
አትጠጣ ራስክን አትላጭ ጥ
ፍርህን አትቀረጥ በስንዴ በ
ወይን አስታዝት ብሎ ። እንዲ
ህ ሁኖ ሲኖር። አብርሃም ላም
ስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራ
ቱን ነገሥተ ከሎዶጎሞርን ድ
ል ነሥቶ ሲመለስ ደስ በሊው
በመዋዕልየኑ ትፈኑ ታለክ ወ
ሚመ ታርእየኒሁ ኪያሃ ዕለተ
አው አልቦ አለው። እሱንስ
አታየውም ምሳሌውን ታያለህ
ና ሑር ዕድም ለዮርዳኖስ። ዮ
ርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው
ዮርዳኖስን ተሻግሮ ቢሄድ መ
ልከ ጼዴቅ ጎብስተ በረከት
ጽዋዓ አኰቴት ይዘ ተቀብሎ
ታል ፣ መልከ ጼዴቅ የቀሳው
ስት አብርሃም የምዕመናን ጎ
ብስት የሥጋው ጽዋዕ የደመ
ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ።
በዚህ ጊዜ መልከ ጼዴቅ ወ
ርቁን ዕጣኑን ከርቤውን ለአብ
ርሃም ሰጠው። ከአብርሃም ለይ
ስሐቅ ከይስሐቅ ለያዕቆብ ደ
ርሰዋል ያዕቆብ ወደግብፅ ሲወ
ርድ ይዘት ወርዷል ሲወጣ
ም ይዘት ወጥቷል። ከያዕቆብ
ሲወርድ ሲዋረድ ከዕሤይ ደ
ርሰዋል ፣ ከዕሤይ ለዳዊት ከዳ
ዊት ለሰሎሞን ከሰሎሞን ለ
ሮብዓም ደርሰዋል። በሮብዓም
ጊዜ መንግሥት ከሁለት ተከ
ፈለ ፣ ኢዮርብዓም ወልደ ናባጥ
ባሥሩ ነገድ በሰማርያ። ሮብዓ
ም በሁለቱ ነገድ በኢየሩ
ሳሌም ነገሡ ሁለቱ ቢጣሉ
ሱስቀም ንጉሠ ግብፅ ለኢዮ
ርብዓም ረፃት ሁኖ ከጥቶ
ሮብዓምን ወግቶ ግብፅ ይ
ዘት ወርዷል ፣ ይህም ብቻ አ
ይደለ ፣ ሰሎሞን ወደ ቤተ እግ
ዚአብሔር ሲገባ ብላቴኖቹ ይ
ዘው የሚከተሉት ሶስት መቶ
የወርቅ ጋሻ ሶስት መቶ የወር
ቅ ጦር የወርቅ ሾተል አሠርቶ
ነበር ይህን ሁሉ አውርዶታል ።
ከግብጽ ባቢሎን እንደምን ይ
ወርዳል ቢሉ ናቡከደነፆር ፈር
ዖን ኒካውን ገድሎ ሶስት ዓመት
ባቢሎን ዘግብፅ አሰኝቶ ሲሄድ
ከግብፅ ባቢሎን ይዘት ወርዷ
ል ፣ ከዚያ አግኝተው ይዘው መ
ጥተዋል። ሊረዳውስ መጥቶ አ
ይወስድበትም አሕዛብ የሰው
ከብት ናቂዎች ናቸውና ብሎ
ሮብዓምን ወግቶ ለኢዮርብዓ
ም ሰጥቶት ይሄዳል። ኢዮርብ
ዓም ከኢየሩሳሌም ሰማርያ ይ
ዘት ወርዷል። ስልምናሶር ዓ
ሥሩን ነገድ በማረከ ጊዜ ፋ
ርስ ባቢሎን ይዘት ወርድዋል
ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥ
ተዋል። አንድም አሜስያስ በሁ
ለቱ ነገድ በኢየሩሳሌም ዮአ
ስ ባሥሩ ነገድ በሰማርያ ነገ
ሡ ፣ አሜስያስ ንጉሠ ኤዶም
ያስን ወግቶ ሲመለስ ኃይል
ቢሰማው ነዓ ንትረዓይ ገጸ በ
ገጽ ብሎ በዮአስ ላከበት። እ
ሱም እስመሁ ሞዕከሙ ለኤ
ዶምያስ ተዝጎረኑ ልብከ ፣ አቃኒ
ዘውስተ ዕፅ ለአከት ኅበ ዕፀ
ወ ቄድሮስ እንዘ ትብል ሀበ
ወለተከ ለወልድየ ፣ ወመጽኡ
ዓራዊት ገዳም ወኬድዋ ለዓቃ
ኒ ብሎ ገሥግሦ ሂዶ ገጠመ
ው ድል አድርጎታል በአንቀጸ
ኤፍሬም አራት መቶ ከንድ አ
ደባባይ አለ በዚያ አስጎትቶ
ታል ነገሥተ እስራኤል ኃያላ
ን ነን ነገሥተ ይሁዳ ድኩማ
ን ናቸው ሲል። በዚህ ጊዜ ከ

ወንጌል ዘማቴዎስ

ኢየሩሳሌም ሰማርያ አውርዶታል። ከሰማርያ ስልሳናሶር ዓምራን ነገድ በማረከ ጊዜ ፋርስ አውርዶታል። ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል። ይህማ እንዳይሆን ዘአንበለ ያእምር ልቦን ስምየ አቡሁ ወእሙ ይሜእ ነያለ ደማስቆ ወምሀር ቅሮርያ ይትካፈል ይላልሳ ቤ ሎ ወርቁ እንጂ ብዙ ነው ከ ዚያም ከዚያም ደርሱዋል። አ ንድም አሣ በሁለቱ ነገድ፡ በ እስ በዓሥሩ ነገድ ነግሠው ሳ ሎ የአሳ። ሬማ የምትባል መው ጫ መግቢያ ነበረችው። ባአስ ጊዮ ቀጸረበት በዚህ አዝኖ ሳ ለ በዚህን ታዝናለህ ከወልደ እዴር ጋራ ሊወጋህ ተማምሎ ብሃል አሉት። ጎድግአ ኪዳነ ሙተከየድከ ምስለ በአስ ብሎ ከዜተ እግዚአብሔር ዕቃቤት ከዜተ መንግሥት ዕቃቤት የተ ገኘውን ወርቅ ጨምሮ ለወል ዶ አዴር ወልዶ ጤዲርማን ወ ልዶ አዚን ወልዶ አዛሄል ንጉ ሥ ሶርያ ይሰድለታል በዚህ ጊ ዜ ሶርያ ይወርዳል። አንድም ኢዮአስ በሁለቱ ነገድ ነግሦ ሳለ አዛሄል ሰባት ያህል አጎ ጉር ወግቶ መጥቶ ከዳር ሰፍ ሮ ገብር አለው። አቱአ እግዚ እየ ዘአየርከኒ እፀውር ብሎ ከ ቤተ እግዚአብሔር ዕቃቤት ከ ቤተ መንግሥት ዕቃቤት የተገ ኘውን ወርቅ ሰዶለታል ሶርያ ይወርዳል። ከሶርያ ፋርስ ባቢ ሎን እንደምን ይወርዳል ቢሉ ቲልጌልቴልፈልሶር በፋርስ ረ ዓሶን በሶርያ ፋቁሄ ወልዶ ሮ ሚልዩ በሰማርያ አካዝ በኢየሩ ሳሌም ነግሠዋል በሶርያና በሰ ማርያ መካከል ሬማት ዘገለዓ ድ የምትባል አገር አለች የ ሶርያው ሲበረታ ወደሶርያ የ ሰማርያው ሲበረታ ወደ ሰማ ርያ የምትገዛ እንደ ዋግ ያ ለች ናት ዋግ የትግሬው ሲ በረታ ወደ ትግሬ የበጌምድሩ ሲበረታ ወደ በጌምድር ትገዛ እንደ ነበረ፡በዚህ ጊዜ በፋቁ ሄ እጅ ንበረች። እሱም ይህች ን አገር ላንተ እሰጥሃለሁ ላባ ቶቹ ሲገዙ የነበሩ ሁለቱ ነገ ድ አምጸውብኛልና እነዚያን አስገዛኝ ብሎ ከረዓሶን ላከበ ት በዚህ ተማምለው ሁለቱ አ ንድ ሁነው ወደ ኢየሩሳሌም ዘመቱ። ወሶበ ሰምዓ ዘንቱ ዳ ዊት ደንገፀት ነፍሱ ወነፍሰ ዙሉ ሕዝቡ እንዲል። አካዝ ይህን ሰምቶ ገብርከኒ ወወል ድከኒ። በግድ ባሯህ በፈቃድ ልጅህ ነኝና። እርዳኝ ብሎ ከቲ ልጌልቴልፈልሶር ዘንድ ላከበ ት እሱም ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ ዘመተ። ሶርያ ሲደ ርስ ይህች አገር የማናት ብሎ ጠየቀ የረአሶን አሉት። እሱ ወዴት ሂዴል አለ አካዝን ሊ ወጋ ኢየሩሳሌም ሂዴል አሉ ት የአካዝን ብላቴና ጥሩ ብሎ አስጠርቶ ጌታህ እርዳኝ ብሎ የላከብኝ ወዴት ድረስ ነው አ ለው። ኢየሩሳሌም ድረስ አለ ው። ልጅ እንጂ ቢሆን የጦር መላ ቢያውቅ ፅው ብሎ ተኩ ስ ዝረፍ አለ። የቆጡን አወ ርድ ብላ የብብቷን ጣለች አ ንዲሉ። የሰው አገር እንወጋለ ን ብላችሁ አገራችሁ ተወጋ ላችሁ አሏቸው። ተመልሰው ገጠሙት ረዓሶን በነፍጥ ተ መቶ ከዚያው ሙቷል። ፋቁሄ ተመቶ ካገሩ ይሞታል። በዚህ ጊዜ ቴልጌልቴልፈልሶር ከሰ ርያ ፋርስ አውርዶታል። ከዚያ አግኝተው ይዘው መጥተዋል አምጥተው ለእመቤታችን ሰ ዊት። እመቤታችንም ተቀብላ ከፍላ ለነዳያን መጽውታለት ለቅዱስ ጴጥሮስ ሰጥታዋለች ቅዱስ ጴጥሮስም ከፍሎ ለነዳ ያን መጽውቶለት ለቀሌምንጦ ስ ሰጥቶታል ቀሌምንጦስ ከፍ ሎ ለነዳያን መጽውቶለት ከስ ምንቱ መጻሕፍት ጋራ በእን ቀጸ ሮም ቀብሮታል። እነዚህስ ምን ጊዜ ተነሥተው ምን ጊዜ ደርሰዋል ቢሉ ለልደት ሁለ ት ዓመት ሲቀረው ተነሥተ ው የልደት ለት ደርሰዋል ይ ህ በምን ይታወቃል ቢሉ ኤ ፏንዮስ ዮም ተወልደ ይላ ልና። ይህማ እንዳይሆን እመቤ ታችን ሰብአ ስገልን ሸኝታ አ ልዋለችም አላደረችም ወዲያ ው መንገድ ጀመረች ይላል በስምንት ቀን ቤተ ግዝረት መግባት ባርባ ቀን ዕጕለ ር ግብ ዘውገ ማዕጠት ይዞ ቤተ መቅደስ መግባት ይቀር የለም ቢሉ አይቀርም። ቄሣር በግብር ምክንያት አስጠርቶት ሮም ሁ ለት ዓመት ኑሮ ይመለሣል ከዚያ በኋላ ነገሩን ያነሳዋል አንድም መንፈስ ቅዱስ ሁ ለት ዓመት ነገሩን አዘንግቶት ከዚህ በኋላ ያነሣዋል። አንድም የልደት ዕለት ተነሥተው በሁ ለት ዓመት ደርሰዋል። ወሠሊ

ሙ· ግብሮ· አተዉ ሀገ
ሮ· ናዝሬት ይላል። ወዴት
አግኝተው ይሰዉታል ቢሉ በ
አድባረ ሊባኖስ ሳለች ባመት
ባመት ለገቢረ በዓል ትወጣ
ነበርና ከዚያ አግኝተው ይሰ
ዉታል። ኤጲፋንዮስ ዮም ተ
ወልደ ይላልሳ ቢሉ እንደ ዛሬ
ደብተራ ባመት ባመቱ ዮም
ተወልደ እንዲል።

ወርቅ ያመጣ የሴም ወገን ነው
መንግሥት ከሴም ወገን ነው
ና ። ዕጣን ያመጣ የያፌት ወገ
ን ነው ከሀናት ከያፌት ወገ
ን ይበዛሉና ። ከርቤ ያመጣ የካም
ወገን ነው ፡ ምዕመናን ከካም
ወገን ይበዛሉና ። ወርቅ ያመ
ጣ የኻያ ዓመት ነው ፡ መንግ
ት ከዚህ በላይ በ፵ ዘመን ያገ
ባል ለማለት ። ዕጣን ያመጣ ያ
ርባ ዘመን ነው መንፈሳዊ ሹ
መት ከዚህ በላይ በምሳ ዘመን
ይገባል ለማለት ። ከርቤ ያመጣ
የ፰ ዘመን ነው ከዚህ በላይ ሞ
ት ያጠራጥራልና ። ለነዚህም ለ
ሕፃኑ በአምሳለ ሕፃን ለወሬዛ
ው በአምሳለ ወሬዛ ፡ ለአረጋዊ
ው በአምሳለ አረጋዊ ታይታ
ቸዋል ወጥተው ሲሄዱ እን
ዱ መልክም ብላቴና አለ ። መ
ልክም ጕልማሳ እንጂ ። መልክ
ም አረጋዊ እንጂ ተባብለው
ተመልሰው ቢገቡ በአምሳለ ሕ
ፃን ለታየው በአምሳለ ወሬዛ
በአምሳለ ወሬዛ ለታየው በ
አምሳለ አረጋዊ በአምሳለ
አረጋዊ ለታየው በአምሳለ
ሕፃን ታይቷቸዋል ። ከዚህ
በኋላ ወጥተው ነገር እንዳ
ንተ መልክም ብላቴና አ
ለው ። እንዳንተ መልክም ጕል
ማሳ እንጂ እንዳንተ መልክም
አረጋዊ እንጂ ። ተባብለዋል ።
መልአኩ እንደሁላችሁም ነው
አትጣሉ አላቸው ። ማየትንስ ሙ
ስግት አያስረዳውም ብለው ተ
መልሰው ቢገቡ በአምሳለ ሕ
ፃን ለታየው በአምሳለ አረጋዊ
በአምሳለ አረጋዊ ለታየው በአ
ምሳለ ወሬዛ በአምሳለ ወሬዛ ለ
ታየው በአምሳለ ሕፃን ታይቷቸ
ው ለሁሉም ሶስት ሶስት ሙል
ክ ደርሷቸው ፍጹም አምላክ
ነቱን በዚህ ተረድተው ሂደዋ
ል ። እነዚህስ ከብር አላቸው ቢ
ሉ የላቸውም ። ዕድግተ በለዓ
ም ዕብነ ሦፃዕን እንዳናገረ
የታምራት ነው ፡ ይህማ እንዳ
ይሆን እመቦ ዘአክበረ ልደተ
እግዚአ ይክውን ክብሩ ምስለ
ሰብአ ሰገል ይላልሳ ብሎ ክብ
ር ያላቸው ናቸው ይህም ሊታ
ወቅ ወአስነቀቶሙ ጎብስተ ሰ
ገም ይላል እመቤታችን ፈሪ
ፀ ሰገም ስንቅ ሰጥታ ሰደደቻ
ቸው ዕልፍ ልዕፍ ሠራዊት እ
የተመገበለት ባያልቅ አገራቸ
ው ሲደርሱ ደግን ነገር ከከተ
ማ ፡ ይዘ መግባት አይገባም ብ
ለው ከከተማ በአፍአ ትተውት
ገቡ ፡ ደርሳችሁ መጣችሁን አሏ
ቸው ፡ አምን አሉ ። ምን ምልክ
ት አላችሁ አሏቸው ፡ እነሱም
ምልክታቸውን እንዲህ ብለው
ተናገሩ ሁለት ዓመት የሄድነ
ው በ፵ ቀን ገባን እናቱ ስንቅ
ሰጥታን ይህ ሁሉ ሠራዊት እየ
ተመገበው ባያልቅ ከቡር ነገር
ነውና ከከተማ ይዘ መግባት
አይገባም ብለን በአፍአ ትተ
ነው መጥተናል አሏቸው ።
አስኪ አሳዩን አላቸው ። ቢሄ
ዱ ሲጤስ ሲነድ ተገኝቷል ።
ከዚህ የትነሣ በአሳት እንጂ
አምልኩ ሲለን ነው ብለው
አሳት የሚያመልኩ ሁነዋል ።
ናትናኤል ሀገረ ስብከቱ ከዚ
ያ ነውና ። ይኸስ የታምራት
ነው ሰማዩን ምድሩን ባሕሩን
የብሱን በፈጠረ በእግዚአብ
ሔር እመኑ ብሎ አስተምሮ
አሳምኖ አጥምቋቸዋልና ከብር
ያላቸው ናቸው፤

፲፪ ወነገሮሙ በህልም ከመ አይግ
ብኡ ኀበ ሄሮድስ ።

፲፫ በሄሮድስ ዘንድ እንዳይመለሱ
በራእይ ነገራቸው ። ከነገ ከሠ
ልስት ይመጣሉ ሲል እመቤ
ታችን መንገድ እንድትገፋ ሃ
ይማኖት እንዲሰፋ ። በመጡበት
የተመለሱ እንደ ሆነ ሃይማኖ
ት ይጸናል እንጂ ። አይሰፋም
ባልመጡበት ቢመለሱ ግን ያ
ልሰማው እየሰማ ይሰፋልና ።
አንድ መንገድ እንዲቀርባቸው
ሁለት ዓመት የመጡትን በ፵
ቀን ገቡ የሚል ነውና ።
ወእንተ ከልዕ ፍኖት ገብኡ ወ
አተዉ ብሔሮሙ ።
በሌላ ጎዳና በሌላ ኃይለ ቃል
በሌላ ሃይማኖት ወደ ሀገራቸው
ተመልሰው ገቡ ። በሌላ ጎዳ
ና ሁለት ዓመት የሄዱትን በ፵
ቀን ገብተዋል ። በሌላ ኃይለ ቃ
ል አይቴ ሀሎ እያሉ መጥተ
ው ነበር ። ረከብናሁ እያሉ ተ
መልሰዋል በሌላ ሃይማኖት ን
ጉሥ እያሉ መጥተው ነበር አ
ምላክ እያሉ ተመልሰዋል ።

ዘከመ ጕየ ውስተ ምድረ ግብፅ
፲፫ ወእምድኅረ ኃለፉ እሉ ናሁ
መልአክ እግዚአብሔር አስተ
ርአዮ በሕልም ለዮሴፍ። ወእ
ንተ ካልዕ ፍኖት ገብኡወአ
ተዉ ብሔሮሙ ብሎ ነበርና
፲፬ ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ ከአ
ግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ
ለዮሴፍ በሕልም ነገረው።ሳሉ
አለመንገሩ ከሄዱ በኋላ መን
ገሩ ስለምን ነው ቢሉ።ሰብአ
ሰገል ሳሉ ነግሮት ቢሆን ሲ
ሰደድ አይተው አምላክነቱን
በተጠራጠሩ ነበርና።አንድም
ካልቀረስ ይዘነው እንሂድ ባሉ
ነበርና። ይዘውትም እንዳይሄዱ
የጌታ ስደቱ ወደ ግብፅ ነው እ
ንጂ።ወደ ባቢሎን አይደለምና።
እንዘ ይብል ተንሥእ ወንሣእ
ሕፃነ ወእሞ ወጕየይ ውስተ
ምድረ ግብፅ። ተነሥተህ
እናቱን ብላቴናውን ይዘህ ወደ
ግብፅ ሂድ ብሎ ነገረው ሐተ
ታ።ሕፃነ ወእሞ አለ ሕፃነ ብሎ
እሞን ቢተው ብላቴናውን አ
ለኝ እንጂ እናቱን አለኝ ባለ
ነበርና፡እሞ ብሎ ሕፃነ ባይል
እናቱን አለኝ እንጂ ብላቴና
ውን አለኝ ባለ ነበርና ሕፃነ
ወእሞ አለ።ጲላጦስ የሆነ
እንደሆነ አመልክቶ ይተዋል
ለመልአክ ግን አከቶ መናገር ል
ማድ ነውና ሕፃነ ወእሞ አለ።
ወሀቡ.ሀየ እስከ አመ እነግረከ
ተመለስ ብዬ እስክነግርህ ከዚ
ያ ኑር አለው።
እስመ ሀለዎ ለሄሮድስ ይኅሥ
ሦ ለሕፃን ከመ ይቅትሎ።
ሄሮድስ ብላቴናውን ሊገድለ
ው ይሻው ዘንድ አለውና።
፲፱ ወተንሢኦ ነሥአ ሕፃነ ወእሞ
በሌሊት ወሖረ ውስተ ብሔረ
ግብፅ።
፳፤ ተነሥቶ ብላቴናውን እናቱን
ይዘ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ
ከብላይ ለልግዱ መንገዱ ሌሊ
ት ነውና።አንድም ወዲያው እ
ንደነገረው ሳያንተላክስ ሄደ
ሱል ሖረ በሌሊት አለ፡
፳፩ ወነበረ ሀየ እስከ አመ ሞቱ
ለሄሮድስ።ሆሴዕ፤፲፩ ፩
፳፪ ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ ፫ት
ዓመት ከመንፈቅ በግብፅ ኖረ።
ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ እም
ኀበ እግዚአብሔር በነቢይ እ
ንዘ ይብል እምግብፅ ጸዋዕኩም
ለወልድየ፡
እግዚአብሔር በነቢይ አድሮ ነ
ቢያ ከእግዚአብሔር ተገልጾ
ለት በነቢዩ ቃል ልጄን ከግብ
ፅ ጠራሁት ተብሎ የተነገረው
ይደርስ ያፈጸም ዘንድ።ሐተታ
ይህግ መውጣቱን ያስረዳል እ
ንጂ መውረዱን ያስረዳልን ቢ
ሉ ከልወረደ መውጣትን አለ
አንድም እም ቅሉ ወደ ሲሆ
ን ነው፡ተጸውዑ እምቴምፍሱ
ስ ጽውዓን እምሰግይ እንዲል
ልጄን ወደ ግብፅ ጠራሁት ተ
ብሎ የተነገረው ይደርስ ይፈ
ጸም ዘንድ፡ወደ ግብፅ ያደረ
ው ስለምን ቢሉ ትንቢቱ ም
ሳሌው ሊደርስ ሊፈጸም፡ትን
ቢት ናሁ እወዲ እይየ ውስ
ተ ምድረ ጳብፅ፡ወትከውን አ
ሕቲ ሀገር ምሥዋዖ ለእግዚአ
ብሔር ይላል ደብረ ቍስቋም
ም እስክንድርያም ቢሉ፡ወደ
ወርድ እግዚእነ ውስተ ምድ
ረ ግብጽ እንዘ ይጼንን ዲቤ
ደመና ቀሊል፡እምግብጽ ጸው
ዕክዎ ለወልድየ ተብሎ ተነግ
ሯል።ይህግ የተነገረ ሰያዕቆብ
አይደለም ቢሉ ለጊዜው ለያዕ
ቆብ ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ ነ
ውና፡ነቢየ ያነሥእ ለክሙ እም
አኃዊክሙ ያለው ለኢያሱ ቢ
ሆን ፍጻሜው ለጌታ እንደሆነ።
ምሳሌም አበቶቹ ወደ ግብፅ
ተሰደዋል ትንቢቱን አውቆ አ
ናግሯል።ምሳሌውንም እንጂ ባ
ወቀ አስመስሏል ፍጻሜው እ
ንደምነው ቢሉ ግብፅ ታቀር
በዋለችና ይሹታልና ለፍቅሩ ይ
ሳሳሉና።ከሀዲት በነዚህ ጸንቶ
ነበርና።ወደ ጸናበትም መሄድ
ልማድ ነው።አሁን በመዋዕለ
ስብከቱ ደቂ ወደ ጸናበቦው
ወደ ጌርጌሴናን ሄደ ብሎ እ
ንዲያመጣው።አንድም ገላግ
ተ ግብፅን ለመባረክ ደጋጉ ገ
ዳግት እነሲሐት እነ ኤስቴተ
ስ ከዚያ አሉና።አንድም መ
ልኩን አይተው የሚያምኑ
አሉና።ወተበህላ አሞልዶ ቈሐ
ት ንው ንርአዮ ለወልደ መን
ክራት እንዲል፡አንድም ኪዳ
ነ መልክ ጼደቅን ለመፈጸም
ዘመዶቿን ማርልኝ ቢለው ል
ጄን በሥጋ ሰደጀ እምርልሃ
ለሁ ብሎት ነበርና።አንድም
ሃይማኖት ከሁሉ ሲጠፉ በ
ግብፅ አይጠፋምና፡እስከ ም
ጽአት ድረስ ወልድ ዋህድ
ስትል ትኖራለችና።ብዚያውስ
ላይ መሰደዱ ስለምነው ቢሉ
እንዳይሞት ጊዜው አልደረሰም
ና ከዚያ ሳለ ድኖም ቢሆን ምት
ሐት ነው ባሉ ነበርና።እንጂ

ም አሳም ከዚህ ዓለም አፍአ ከምትሆን ከንነት ተሰዶ ነበርና ለዚያ እንደ ካሰ ለማወየቅ። እንድም ሊሰማዕታት ስደትን ለመባረክ ሰማዕትነት ብቻ በእሳት በስለት እደደለም። እገር ንም ጥሎ መሰደድ ስማዕትነት ነውና። እንድም ጉየተ ሕፃን አጉየቦ ለዲያብሎስ እንዲ ል። ኢጋንንትን ከሰው ልቡና አስወጥቶ ለመስደድ።

በእንተ ሚጠት እምነ ግብፅ።

፲፯ መሰበ ርእየ ኔርድስ ከመ ተ ግለቃ ላዕሌሁ ሰብኤ ሰገል ተ
፲፰ ምን ጥቀ።

ሄርድስ እንደዘዘቱበት ባየ ጊዜ ግልት ጠንቶ በዙል እንመለ ሰልን ብለው በሌላ ጎዳና እን ደሄዱ በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ተበ ሳጨ። በማን ደበሳጫል ቢሉ ብስጩ ለልማዱ ዘልጋው በመከሰው በቤተ ሰቡ የጨለማ ገልማጭ እንዲሉ።

ወእዘዘ ሐራሁ ወረነወ ደቅት ሉ ዙሉ ሕፃናተ ዘቤተ ልሔ ም ወዘዙሉ አድያሂሃ።

በቤተ ልሔም ባው-ራጆዋ ያሉ ሕፃናትን ሁሉ ገደሉ ብሎ አ ዝዘ ሰደደ። ዘሄኤ ዓመት፤ መዘይንዕስሂ እምኔሁ።

ዓመት ከመንፈቅ፣ዓመት የሆ ነው-ንም፣

በከመ ሐሳበ መዋዕል ዘተጠ የቀ እምኀበ ሰብአ ሰገል፤ ከሰብአ ሰገል ጠይቆ በተረዳ ው ዘመን ልክ፤

፲፱ አሜሃ ተረጸመ ዘተብህለ በ ኤርምያስ ነቢይ እንዘ ይብል
፳ ቃል ተሰምዓ በራማ።

ያን ጊዜ ኤርምያስ ቃል በራ ማ ተሰማ ብሎ የተናገረው ት ንቢት ደረሰ ተፈጸመ ይደርስ ይፈጸም ዘንድ አዘዘ፤ ራማ በ ቁሙ ሰማይ፤ አንድም ከፍ ባለ ቦታ፤ አንድም በመላእክት ዘን ድ፤ አንድም በእግዚአብሔር ዘ ንድ፤ ብካይ፤

የልጆቻቸው ከናቶቻቸው ሲለ ይዋቸው፣

ወሰቆቃው፣

የናቶቻቸው፤

ወግዓር፤

የልጆቹ ጠምዘው ሊያርዱቸው ወሕግም ብዙኅ ይላል ፱ ወር ከምስት ቀን የፀነሰ ግሕፀን አ ይችልምና፣

፳፩ ራሄል እንዘ ትበኪ በእንተ ው ሉዳ፣ኤር ፴፩ ፲፫፣

፳፪ ራሄል ለልጆችዋ ስታለቅስ ተሰ ማ ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘ ንድ አዘዘ። አንድም ደረሰ ተ ፈጸመ፤ ሐተታ፤

ልያን አላሄሃ ራሄል አለ ምነ ው ቢሉ የልያ ዕጻዋ ነው ጌታ ከሷ ወገን ተወልዱልና፣የራ ሄል ግን ያለዕጻዋ ነው ጌታ ከሷ ወገን አያወለድምና፣አን ድም የልያ በርኅቱተ ሀገር በ ብዛት ድንግላታል የራሄል ግን ቢማነስ በቅርብ አልቀመጣታል ና። አንድም በራሄል ልያን መናገር ነው። አንድም እናታ ችን ራሄል ኑራልን መከራ ችነን አይታ አልቅሳልን ብለ ው ስላለቀሱ፣ አንድም እንድ ናለን መስሏቸው ከመቃብረ ራሄል ገበተዋል ከዚያ እየ ገቡ ፈጅተዋቸዋልና። አንድም በራሄል ሁሉን መናገር ነው

ይሁግ እከፍሉ ውስተ ያዕቆብ ወእዘርዎ ውስተ እስራኤል እ ንዲል፣ሁሉን በሚያገናኝ በያ ዕቆብ ባልተናገረውም ነበር ቢሉ፣ወንድ ልጅ ለፈረሰ ሴት ልጅ ለበርናስ ከደረሱ በኋላ የሞቱ እንደሆነ ኃዘን በባት ይጸናል በሕፃንነት የሞቱ እን ደሆነ ግን ኃዘን በናት ይጸና ልና በሚጸናው ተናገረ። አን ድም ግፍ ለግፍ ሲያንጸባርር የ ቀደመችቱ ራሄል የምትበል ሴት ባፅ ርሔልም ስምዖንም ይባላል በሷ ሙቶ በባሷ ስፍራ ፍራ እርገጭ ብለዋት ስትረግ ጥ መንታ ወንሳ ኑራ ወጥተው ወጥተው ወደቁ ደንግጣ ቆመ ች የሰው ሥጋ ያጸናዋል እንጂ ምን ይለዋል እርገጭ አሷት ኢ።ሱኑ በዝ ሰማይ አምላክ እስራኤል ብላ እንባዋን በእ ጁዋ ተቀብላ ወደ ላይ ረጭ ተዋለች፣ሰማዕኩ ገሥርሙ ለ ሕዝብየ ወወረድኩ ከመ አድ ኅኖሙ ያሰኘው ይህ ነው። አ ንድም ራሄል መንግሥተ ሰማይ የሚገባበት አጥታ ታዝናለች ታለቅሳለች።

መዓበየት ተናገዘ ወኀፈ ላህ ራሄል ልቅሶ መተውን መጽ ናናትን እምቢ አለች። ላፉ ያ ሳዝናልና የያር ሞት ነውና ጎ ዘን በየደጁ ሁኑአልና።

እስመ ኢኮንዋ ውሉዳ ውሉደ ልጆቹአ ልጆች አልሆኑአት ምና መተዋልና ማለት ነው። አንድም እስመ ኢኮኑ ውሉ ደ። ልጆቹአ አይደሉምና የተ ውሰ ናቸውና።

ወኢሀለዉ።

በሕይወት ሥጋም የሉምና።
ሐተታ፡እነዚህንስ እንደምን አድርጎ ይሰበስባቸዋል ቢሉ ቄሣር ሕፃናትን ሰብስበህ ል ብስ ምግብ እየሰጠህ በማር በወተት አስድገህ ለናት ለ ባታቸው ርስት ጉልት እየሰ ጠህ ጭፍራ ስራልኝ ብሎኛ ል ብሎ አዋጅ ነገረ። ያላት ልጁዋን የሌላት ልብስ ምግ ብ ልቀበልበት ብላ እያታዋሰች ይዛ ሂዳለች እንዲህ አድርጎ ሰብስቦ ፈጅቷቸዋል፡ ይህስ ዕ ጻው በማን ይሆናል ቢሉ በሱ፡ በደዊት ምክንያት ፲፪ ጽርፈ ቈዋ ውያን ቢያልቁ፡፩ሳሙ ፳፪፡፲፰ በጴጥሮስ ምክንያት ፲፯ት ሰ ገራት ቢያልቁ ግብረ ሐዋ ፲፪፡ ፲፱። ዕጻው በሳአል በሄ ሮድስ ሆነ እንጂ በዳዊት በጴጥ ሮስ ሆነን አሊያስ ባያውቁ ነው እሱማ እያወቀ ቢሉ ያውቃልማ ከሉ ሁሉንም ያውቃል መጠ ቀማቸውንም ያውቃል። ለኢህ ስ ክብር አላቸው፡ ቢሉ የላቸ ውም ይሏል።ይህማ እንዳይሆ ን ስንክሳር ተጽፎላቸው ታቦ ት ተቀርጾላቸው አብያተ ክር ቲያናት ታንጸላቸው የለም ቢሉ ሳያውቁ በሠሩት ሥራ መጠቀም እንደሌለ ለማጠየቅ ነው እንጂ ክብር አላቸው
፲፱ ወ።ዊቶ ሄሮድስ ናሁ መልአ ክ እግዚአብሔር አስተርአ የ በሕልም ለዮሴፍ በብሔረ ግብፅ
፲፱ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በሳብዕ ሳለ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መ ልአክ ለዮሴፍ በህልም ነገረው፡
፳ እንዘ ይብል ተንሥእ ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሖር ውስተ ምድረ እስራኤል።
፳፩ ተነሥተህ ብላቴናውን እናቱን ይዘህ ወደ ምድረ እስራኤል ተመለስ ብሎ ነገረው።
እስሙ ሞቱ እለ የኀሥሥዎ ለነፍሰ ዝ ሕፃን።
የዚህን ብላቴና ሰውነት ለጥ ፋት የሚሹዋት ሰዎች ሙተ ዋልና። ኢትቀትል ነፍሰ እን ዲል።አንድም ነፍስ እንደነሣ ለማጠየቅ ለነፍስ ዝ ሕፃን አለ። ሐተታ፡ምነው የሞተ አንድ ሄሮድስ አይደለም ሞቱ ብሎ አበዛ ቢሉ።የምክር ጋናቸው እሱ ነው እሱ ከሞተ ያነሡ ታልን ብሎ።እንድም በሶስት ዓመት ከመንፈቅ ስንኳን በዓ ላውያን ከተማ በምዕመናን ከ ተማስ እንኳ ብዙ ሰዎች ይሞ ታሉና። እሱንም የመሰሉ ሰዎ ች ሙተዋልና ሞቱ አለ።
፳፩ ወተንሣእ ነሥአ ሕፃነ ወእሞ ወበዓ ውስተ ምድረ እስራኤል
፳፩ ፡ነገሥቶ ብላቴናውን እናቱን ይዘ ወደ ምድረ እስራኤል ተ መለሰ።
፳፪ ወሰሚአ ከመ አርኬላዎስ ነግ ሠ ለይሁዳ ህየንተ አቡሁ ሄሮ ድስ ፈርሃ ሖሮረ ህየ።
፳፪ ባባቱ በሄሮድስ ፈንታ ይሁዳን ለመግዛት አርኬላኦስ እንደ ነ ገሠ ሰምቶ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ፈራ።ሐተታ የከፉ ል ጅ ከፉ እሱስ ያባቱን ከፋት ይተውናል ብሎ።እንድም ል ጆቻቸው የሞቱባቸው የይሁዳ ሰዎች ልጆቻችን ያለቁ በንተ ልጅ ምክንያት አደደለም ብለ ው ቢጣሉኝሳ ብሎ ደም ፈራ።
ወእስተርአዮ በሕልም፡ በሕ ልም ነገረው።
ወተግኀሠ ውስተ ደወለ ገሊላ ገሊላ ገባ፡ገኀሠ አጋእዝትየ እንዲል።
፳፫ ወበጺሖ ኀደረ ውስተ ብሔር እንተ ስማ ናዝሬት፡
፳፫ ገሊላ ደርሰ ናዝሬት ገብቶ ና ዝሬት በምትባል አገር ኖረ፡ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነ ቢይ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ።
ልጂ እንደ ናዝራዊ እንደ ሶ ምሶን ይባላል ተብሎ በነቢይ ቃል የተነገረው ይደርስ ደፈ ጸም ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖ ረ።ሐተታ እንደህ የሚል ወ ዴት አለ ቢሉ በዜዋዊ ጠፍ ቷል በዜዋዊም እንደ ጠፋ በተግባዘ ሰሎሞን ታውቋል። ይህስ እዝራ ነሥአን ወአስተ ጋብአን ይለዋል ብሎ ተናግ ሮት ሳይጸፍ የቀረ ነው።ተና ገረውት የቀረውን ማምጣት ለሐዋርያት ልማድ ነው።ተዓ ቀቡ በመዋዕለ አፅራር ያለው ን በከመ ይቤ ኢዮብ እንዳሉ እንደ ናዝራዊ እንደ ሶምሶን ይባላል ተብሎ በነቢይ የተነገ ረው ይደርስ ይፈጸም ዘን ድ በናዝሬት ኖረ።ጸም በአሪ ቱ እስመ ናዝራዊ ሐዲስ ውእ ቱ ለእግዚአብሔር ያለውን እንዲህ ለውጦ አነበበው።ይ ህንማ የተናገረ መልአክ አ ይደለም ስለምን ነቢይ አለ ው ቢሉ፡ መልአክ ይሰመይ በእንተ ተልእኮቱ ወሐዋርያ ይሰመይ በእንተ ሐዊሮቱ አ ንዲል፡ከዚያ በግዑሩ መልአ

ከ እንደ አለው ከዚህም በግ
ብሩ ነቢይ አለው። ያውስ ቢ
ሆን ይህ የተነገረ ለሶምሶን
አይደለምን ቢሉ።ለጊዜው ለሶ
ምሶን ቢሆን ፍጻሜው ለጌታ
ነውና።አነ እከውኖ አባሁ ወ
ውእቱ ይከውነኒ ወልድየ ያለ
ው ለጊዜው ለሰሎሞን ቢሆን
ፍጻሜው ለጌታ እንደ ሆነ
ያውስ ቢሆን በምን ይመስለ
ዋልና እንዲህ አለ ቢሉ።ሶም
ሶን በተናቀች መንሰክ አድግ
ጠላቶቹን እንዳጠፋ ጌታም አ
ይሁድ አጋንንት መናፍቃን
በናቁት ሞቱ ሞትን አጥፍቷ
ልና። ሶምሶን በሕይወተ ሥጋ
ሳለ ከጠፋቸው አሕዛብ በሞቱ
ያጠፋቸው ይበዛሉ።ጌታም በ
ሕይወተ ሥጋ ሳለ ከጠፋቸው
አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው
ይበዛሉና።አንድም ከመ ናዝ
ራዌ ይሰመይ ብለህ ናዝሬት
ማለት ፍልጠት ከፍለት ማለት
ነው። ልጂ ልዩ ይባል ዘንድ
ናዝሬት ገብቶ ኖረ።ዘተብህለ
በነቢይ ስሙ ለልዑል ቅዱሰ ቅ
ዱሳን ወይትቀበዕ ቅዱሰ ቅዱሳ
ን ያለው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ
አንድም ናዝሬት ማለት ጎሥ
ርት ማለት ነው፤ይእተ አሚ
ሪ ይሰምያ ለናዝሬት በስመ
ኃጥር እንዲል።ልጂ ጎሠር ይ
ባል ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ
አልህሠር እንዲል በዓረብ
ጎሠር ሲል።አንድም ናዝሬት
ማለት አጽቀ ጽጌ ማለት ነው
ልጂ አጽቅያዊ ጽጌያዊ ይባል
ዘንድ ናዝሬት ገብቶ ኖረ።እሱ
እንደ ጉንድ ናሁ ምዕመናንን
እንደ አዕፁቅ እንደ ጽጌያት
አድርጎ ያስገኛልና፤ያው ግን
በነቢይ ቃል ትወጽእ በትር እ
ምሥርመ ዕሤይ ወየዓርግ ጽጌ
እምጉንዱ ተብሎ የተነገረው
ደደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው።

በእንተ ስብከተ ዮሐንስ።

ምዕራፍ ፫ቱ ፤

፩ ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ዮ
ሐንስ መጥምቅ እንዘ ይሰብክ
በገዳመ ይሁዳ ዘዮርዳኖስ፤
፪ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ ወልድየ
ብሎ ነበርና ናዝራዊ በተባለበ
ት ወራት፤ቦአ ናዝሬተ ብሎ
ነበርና ናዝሬት በገባበት ወራ
ት፤ሐያ አምስቱን ዘመን አንድ
ወገን አድርጎ ወበውእቱ መዋ
ዕል አለ በዮሐንስ አርባውን
ቀን እንዳንድ ቀን አድርጎ ወ
አመ ሳኒታ እንዳለ። አንድም
ወተወሊዶ ብሎ ነበርና ሥጋ
በሆነበት ወራት።አንድም ለዮ
ሐንስ ሠላሳ ሲመላው ለጌታ
መንፈቅ ሲቀረው በዚያ ወራ
ት የዮርዳኖስ አውራጃ በምት
ሆን በይሁዳ ምድረ በዳ ዮሐ
ንስ መጥምቅ ሲያስተምር ደረ
ሰ።በገዳም አለ ቢታው ነውና
አንድም በገዳም እንጨት ሰባ
ሪ ውሀ ቀጂ አይታጣምና።አ
ንድም በገዳም ያር ይቀላል ለ
ወጣንያን አብነት ለመሆን በ
ገዳም ያር ይጸናል።ለፍጹማን
አብነት ለመሆን።አንድም ገዳ
ም የአይሁድ ልቡና ነው።
በገዳም እህል ተከል እንዳይ
ገኝ፤በአይሁድም ልቡና ምግ
ባር ሃይማኖት አይገኝምና።አ
ንድም ኢሳይያስ ቃለ ዓዋዲ
ዘይሰብክ በገዳም ብሎ የተ
ናገረልኝ እኔ ነኝ ሲል።

፫ እንዘ ይብል ነስሑ እስመ ቀር
በት መንግሥተ ሰማያት።ማር
፬፡፪።ሉቃ ፫፡፫።

፬ መንግሥተ ሰማያት በልጅነት
ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ ቀ
ርባለችና እመኑ እያለ ሲያስተ
ምር ደረሰ።

፫ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘተብህለ
በኢሳይያስ ነቢይ እንዘ ይብል
ቃለ ዓዋዲ ዘይሰብክ በገዳም።
ኢሳ ፵፡፫።ማር ፩፡፫።ሉቃ
፫፡፬።

፫ በገዳም የሚያስተምር አዋ
ጅ ነጋሪ ተብሎ በኢሳይያስ
ቃል የተነገረለት ይህ ዮሐንስ
ነውና። ቃለ አዕዋዲ። አዕዋደ
ቃል ይላል ትምርቱን ከዚያም
ከዚያም የሚያደርስ ማለት ነው
ቃል ዓዋዲ ይላል። ይህንንም፤
ቃል ዘይኬልህ በገዳም ብሎ ሊ
ቁ ወስዶታል።

ወይብል ጸሐአ ፍኖቶ ለእግ
ዚአብሔር። የእግ
ዚአብሔርን መንገድ ጽረጉ።
ወርቱዓ ግበሩ መጽያሕቶ።
ጽርጊያውን የቀና አድርጉ እያ
ለ ሲያስተምር ደረሰ።ሐተታ።
ንጉሥ በመጣ ጊዜ ተራራው
ከረብታው ተንዶ ጉድጓዳው
መልቶ ሥራ ተነቅሎ ደንያጊው
ተለቅሞ ለፈረስ ለሠረገላ እን
ዲመች ተደልድሎ ይቂያልና
በዚያ ግሥ ተናገረው። የእግዚ
አብሔር ማደሪያ ሰውነታችሁ
ን ከኃጢአት ከጣዖት ንጹሕ
አድርጉ።

፬ ወልብሱ ለዮሐንስ ከነ እምፀጉ
ረ ገመል።

ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተ
ማሩ ነገሥታት እንጂ ካፓ ላን
ቃ ያልብሱኝ ብሎ ነው ትሉኝ
እንደሆነ ፡ ይህ ለሥጋውያን
ነው ።እሱ ግን መንፈሳዊ ነውና
፭ ይህን አይሸም ።ዮሐንስስ የሚ
ለብሰው የገመል ጠጕር ነበር ።
ሐተታ ። ገመል ምን ጠጕር አላ
ትና ቢሉ ከጋማዋ ከጅራቷ ቢ
ፈልጉ አያታጣም ልብሱን ሲ
ል ወምበዴ ይጣላዋል ብላ እና
ቱ ያነን እሠርታ አልብሳው ነበ
ር ። እንድም ገመል በቀለኛ ና
ት አጥብቆ የመታትን እስከ ፯
እስከ ፯ዓመት አትዘነጋም ባጥ
ብላ ትረግጠዋለች ስፍራ ሲመ
ቻት ገደል ገፍታ ትጥለዋለች ።
እሱም ወይወድይዎሙ ውስተ
እቶነ እሳት የምትል ሕገ በቀል
ወንጌልን አስተምራለሁ ሲል ።
እንድም ገመል ሁለት ግብር
አላት ። የሚበላና የማይበላ እን
ደ ላምና እንደ በሬ ምንዛኅ ታ
ወጣለች እንደ ፈረስ እንደ በ
ቅሎ ሰኰናዋ ጽፋቅ ነው ።እስ
መ ገመል ጽፋቅ ሰኰናሁ ወያ
መሰኰዕ እንዲል።እሱም ሕገ አ
ሕዛብ ወሕዝብ ወንጌልን አስተ
ምራለሁ ሲል ፤ እንድም ገመሎ
የሚባል ዕፅ አለ ቆርጠው አድ
፮ ርቀው ከባሕር የጣሉት እንደ
ሆነ ጭረት ይወጣዋል ያነን ታ
ትታ አልብሳዋለች ፡ ለጊዜው
ኑሮው በገዳም ነውና ልብሱን
ሲል ወምበዴ እንዳይጣላው
ነው ። ፍጻሜው ግን ለምዕመና
ን አብነት ለመሆን ተርታ ልብ
ስ ለብሳችሁ አልባሌ መስላችሁ
ኑሩ ለማለት ።
ወቅናቱ ዘአዲም ውስተ ሐቄሁ

ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተ
ማሩ ነገሥታት እንጂ የወርቅ
ዝናር ያስታጥቁኝ ብሎ ነው ት
ሉኝ እንደሆነ ። ይህ ለሥጋው
ያን ነው ። እሱ ግን መንፈሳዊ
ነውና ይኸን አይሻም ። እሱስ
ወገቡን የሚታጠቅበት ዓረብ
ነበር ፤ያ ከደመ ነፍስ የተለየ
እንደሆነ፡እሱም ከሥጋዊ ከደ
ማዊ ላብር ልዩ ነኝ ሲል፤ይኸን
አስቀድሞ ከደመ ነፍስ ይለዩታ
ል ከወሀ ይነክሩታል ኋላ ጠጕሩ
ን ይመልጡታል ያለፉታል ቀ
ለም ያገቡታል ፤ ከደመ ነፍስ
እንዲለዩት መክሮ አስተምሮ
ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ይለ
ያቸዋል ፤ ከውሀ እንደ መንከር
ያጠምቃቸዋል ያስተምራቸዋል
እንደ ማልፋት ምግባር ሃይማ
ኖት ያሠራቸዋል ቀለም እንደ
ማግበት ጸጋ ክብር ያሰጣቸ
ዋል ዮሐንስ ግን እንዲህ ማ
ድረጉ ፍትወት እንስሳዊት በባ
ሕርዩ እያለች በገቢር እንዳላወ
ረዳት ያጠይቃል ።
ወሰሳዩ አንበጣ ወመዓረ ገዳም
ዮሐንስማ እንዲህ ብሎ ማስተ
ማሩ ነገሥታት እንጂ ጣቦ ጋቦ
ዶሮ ስቅስቆ ያብሉኝ ብሎ ነው
ትሉኝ እንደ ሆነ ይህ ለሥጋ
ውያን ነው ፤እሱ ግን መንፈሳ
ዊ ነውና ይህን አይሻም ምግ
ቡም አንበጣ የሚባል ቅጠል
ደቁሶ ጨው ነስንሶ ነበር ፤
አንድም አንበጣ በልሳነ አቴ
ና ቀምሲስ ይለዋል በኛም ሰባ
ቦት የጋጃ ማ ይባላል ። ወ
መዓረ ገዳም አለ ።የማን ማ
ር ይሏል ፤አንድም አንበጣ ይ
ላል በቁሙ አንበጣውን ይበላ

ው ነበር ፤በወረቡ አልጀራድ ይ
ላል አንበጣ ሲል ።ሐተታ። በዘ
መኑዋ እያሉ እንድታልፍ ለማ
ጠየቅ አሪትን አይጠቅትም ነ
በር ። በ፷ ቀን ግዘሩ የምትለው
ን ኢያሱ በ፵ ዘመን ገዝሯል ።
ሶምሶን ከአፈ አንበሳ መዓር እ
ግኝቶ ተመግቧል ከመንሰከ አ
ድግ ውሀ ጠጥቷል ። ኤልያስ
ም በአፈ ቋዕ ሥጋ እየመጣለት
ይበላ ነበር ፤ዮሐንስም በቁሙ
አንበጣውን ይበላው ነበር ። ወ
መዓረ ገዳም ባለው ወመዓረ ጸ
ደና ይላል ፤ የጣዝማ ማር ። ይ
ህንም ሊቁ አንበጣ ዘይቤ ልዕ
ልና ስብከቱ ይእቲ ።መዓር ዘ
ይቤ ጣዕመ ስብከቱ ይእቲ
ብሎ ተርጕሞታል ።
፩ ወየሐውሩ ኀቤሁ ኵሎሙ ሰ
ብአ ይሁዳ ወኢየሩሳሌም ወኵ
ሉ አድያሚሃ ለዮርዳኖስ ።
ማር ፩፤ ፭ ።
፮ በኢየሩሳሌም በይሁዳ በዮርዳ
ኖስ አውራጃ ያሉ ሰዎች ሁሉ
ከሱ ዘንድ እየሄዱ ፤
፯ ወያጠምቆሙ ለኵሎሙ በፈ
ለገ ዮርዳኖስ እንዘ ይትአመኑ
ኃጣውኢሆሙ ።
፯ ኃጢአታቸውን እየነገሩት በዮ
ርዳኖስ ያጠምቃቸው ነበር ። እ
ጊሌ ተጠመቅ በማየ ንስሐ ከ
መ ትኩን ረድኦ ለክርስቶስ እ
ያለ ፤ ሐተታ ጥምቀት ከሰስት
ወገን ነው ። መዝገበ ውሉድ ፍ
ቁረን የምትባል የጌታ ጥምቀ
ት ፤ ጥምቀተ ዮሐንስ ጥምቀተ
አይሁድ።ጥምቀተ አይሁድና ጥ
ምቀተ ዮሐንስማ አንድ አይሆ
ንም ሁሉም ልጅነት ያአሰጥ
ቢሉ አንድ አይደለም ከሰውነ

ታቸው ሰውነቱ እንዲበልጥ ፤ ከተመቀታቸውም ጥመቱ ይበልጣል ።አንድም ፷ወገን ነው ፮ቱ ምሳሌ ፮ቱ አማናዊ ።ምሳሌ አጥመቃ ለምድር በማየ አይህ ።ወለዙሎሙ· አበዊነ አጥመቆሙ· ሙሴ በደመና ወበባሕር።ወተጠምቃ እገሪሆሙ· ለክሠናት ያለው ። ጥምቀተ ዮሐንስ፤ ይህ ምሳሌ ነው ። አራቱ አማናዊ መዝገበ ውሉድ ፍቁራን የምትባል የጌታ ጥምቀት አንብዓ ንስሐ፤ደመ ሰማዕት ባሕረ እሳት ።

፯ ወሶበ ርእየ ብዙኀነ አሕዛበ እምረፊሳውያን ወሰዱቃውያን እንዘ ይመጽኡ ውስተ ጥምቀቱ ጽሚተ ።ሉቃ ፫ ፣፯ ።

፯ ከጸሐፍት ከፈሪሳውያን ወገኒ ብዙ ሰዎች ጻድቃን መስለው ኃጢአታቸውን ሠውረው አልባሌ መስለው ተርታ ልብስ ለብሰው የአሪትን መፍረሻ የወንጌልን መታነጫ እና ያለን ብለው እሱ ወደሚያጠምቅበት ሲመጡ ባየ ጊዜ ።ሐ ተታ፤እስራኤል አይደሉም ስለምን አሕዛብ አላቸው ቢሉ ስለብዘታቸው።አንድም በጸያፍ የገባ ግብረ አሕዛብ ይሠራሉና፤ባባታቸው በፋሪስ ፈሪሳውያን በሳዶቅ ሰዱቃውያን ተብለዋል ባባትም ስም መጠራት ልማድ ነው ።በጌበር ፅብራውያን በይሁዳ አይሁድ እንደ ተባሉ ።

ወይቤሎሙ· አትውልደ አራዊተ ምድር መኑ አመረክሙ· ትጕየዩ እመቅሰፍት ወእመንሱት ዘይመጽእ ።

እናንት የፍኝት አባብ ልጆች በነፍስ በሥጋ ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ።እመቅሰፍት ወእመንሱት ወእመዓት ዘይመጽእ ይላል ።በጥሬስ በሐሳዊ መሢሕ በምጽዓት ከሚመጣው መከራ ትድኑ ዘንድ ማን ነገራችሁ ።ሊማሩለት እንዳልመጡ ያውቅ የለምን በሉ የማይጠቀም ከጉባዔው አያመጣምና አንድም የሹም ሰነፍ ባይለፈልፍ እንዲሉ ።ንግር ወኢታር ምም ብሎታልና ።አባቶቻቸው ወደው ባወጡት ስም ትውልደ አራዊተ ምድር አላቸው ። ወንድማቸውን ዮሔፍን ሸጠው በልተው እኩይ አርዌ በልዖ ብለው ነበርና ። ትውልደ አራዊተ ምድር ያላት አርዌ ገሞራዊት ናት አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነው ዘሩን ባኀ ትቀበለዋለች አባለ ዘሩን ቆርጣ ታስቀረዋለች ። በፅንስ ጊዜ አባት ይሞታል በሚወለዱበትም ጊዜ አፈ ማኅፀኑዋ ጠባብ ነውና ሥጋዋን በልተው ሆዷን ቀደው ይወጣሉ ። በዚህ ጊዜ እናት ትሞታለች ። እኒህም እንዳባት የሚሆኑዋቸውን ነቢያትን እንደ እናት የሚሆኑዋቸው ሐዋርያትን ገድለዋልና ። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም እንት ትቀትሎሙ· ለነቢያት ወትዌግሮሙ· ለሐዋርያት እለ ተፈ ;ሠ ·;ቤሃ ብሎ እንዲያመጣው ።

፰ ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሥናየ ዘይደልወክሙ· ለንስሐ ።

፱ ከእንግዲህስ ወዲህ ለማን የሚያበቃችሁን ሥራ ሥሩ ።

፱ ወኢይምሰልክሙ· ዘታመሥጡ በብሂለ ዘትብሉ አብ ብነ ·አብርሃም ። ዮሐ፤፰ ፴፱ ።

፱ አብርሃምን ያህል አባት ሳለን ትውልደ አራዊተ ምድር ይለናል በግለት ትውልደ አራዊቶ ምድር ከመባል የምትድኑ አይምሰላችሁ፤እንዲሉት አውቆ አመጣ እንዲሉትም አውቆ ማምጣትልማድ ነው።ብፅዓን ብፅዓን እያለ ሲያስተምር ሰምተው አሪትን ነቢያትን ሲያሳልፋቸው መጥታል እንዲሉት አውቆ ኢይምሰልክሙ· ዘመጻእኩ አስዓሮሙ· ለአሪት ወነቢያት ዘእንበለ ዳዕሙ· ከመ እፈጽሞሙ· እንጸለ ። ወኢትሁበ ለጻድቅከ ይርአይ ሙስና ቢላቸው፤ይህንማ ጻዊት የተናገረው ለራሱ አይደለም እንዲሉት አውቆ ታበውሁነሁ አሰብእ ንንግርከሙ· ከሠተ በእንተ ጻዊት ርእሰ አበው ቀደምት ከመሂ ሞተ ወ ተቀብረ እንጸለ ። ከዚህም እንዲህ አለ ።

እብለክሙ· ከመ ይክል እግዚአብሔር እምእላንቱ አዕበን እንሥአ ውሉድ ለአብርሃም ፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከነዚህ ከአሕዛብ ልጅ ማስነሳት አቅሞ ውሉድ ይላል መተከት እንዲቻለው ይቻለዋል ብዬ እነግራችኋለሁ፤አንሥአ ውሉድ አንሥአ ውሉደ ይላል ። እላንቱ አላቸው አሁን ያሉ በመከከል ነውና ፤ኋላ ብሔረ ጌርጌሴኖን ገባ ብሎ እንዲያመጣው፤አዕበን አላቸው ደንጊያ ያመልክሉና፤አንድም ያቡስ ነው ይቡሳን እእምሮ ናቸ

ወንጌል ዘማቴዎስ።

ውና፣ ቁሬር ነው ቁሬራን አእ
ምሮ ናቸውና፣ ክቡድ ነው ክ
ቡዳነ አእምሮ ናቸውና።
፲ እስመ ናሁ ተሠይመ ማሕፄ
ውስተ ጦንደ ዕፀው ይንበር፤
፲፩ ምሳር ዓፅቁን ከግንዱ ሊለይ
ተቃጥቷልና፣ ማለት የናንተን
ልጅነት ከአብርሃም አባትነት
ሊለይ ሥልጣነ እግዚአብሔር
ተቃጥቷልና ኢይምሰልክሙ በ
ብሂለ ዘትብሉ ላለው፣ ወንጌል
ሕገ አሕዛብ ወሕዝብ ውና ተ
ሠርታለችና፣ እብለክሙ ከመ
እግዚአብሔር ይክል እንሥአ
ውሉደ ላለው፣ መለከት ከሥ
ጋ ተዋሕዷልና መኑ ኦመረ
ክሙ ላለው ክፉውን ሕሊና
ከበጎ ሕሊና ሊለይ ሥልጣነ
ክህነት ተቃጥቷልና ግብሩኬ
እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወኩ
ሙ ለንሰሐ ላለው፣
ዅሉኬ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠ
ናየ ይገዝምዎ ወውስተ እሳ
ት ይወድይዎ፤
በጎ ፍሬ የማያፈራውን ዕፅ ሁ
ሉ ይቈርጡታል በእሳት ያቃ
ጥሉታል፤ በኔ ትምርት አምኖ
በጎ ሥራ የማይሠራውን ሰው
ሁሉ ነፍሱን ከሥጋው ይለዩ
ታል በገሃነም ሥቃይ ያመጡ
፲፪ በታል፣ አንሰኬ አጠም
ቀክሙ በማይ ለንስሐ፣ ማር፩
፫። ሉቃ ፫ ፲፮ ዮሐ ፩ ፳፯ ግብ
ሐ ፩ ፭። በዚህ ያልተያዘ
በሉቃስ የተያያዘ ነው ባለጸጎች
መጥተው ምንተ ንግበር አሉ
ት። ዘበ ፪ኤ ከዳናት የሀብ ፩
ደ ለዘአልቦቱ ወዘሂ በ እክል
ከማሁ ደግበር አላቸው፤ ኃጥ
አን መጸብሐን መጥተው ም
ንተ፣ ንግበር አሉት። አልቦ ፍ
ድፋዴ ዘትገብሩ እምዘተአዘ
ዝክሙ አላቸው አንበሳ ወደቅ
የወርቅ ተኩስ የግምጃው መ
ከንጃ የላሙን መንጃ እያሉ
የሚወስዱት አላቸውና። የደል
ቄፍረ መጥተው ምንተ ንግ
በር አሉት። ኢትትዓገሉ ወ
ኢትሂዱ መነሂ አላ ንበሩ በ
በሲሳይክሙ አላቸው ዮሐን
ስ እንዲህ ብሎ ማስተማሩ ክር
ስቶስ እንጂ ቢሆን ነው ብለዋ
፲፩ ል እኔስ ለጸጅ ቢረሌን ለልብ
ስ ገላን እንዲያጽቡለት ለሱ
ጥምቀት በሚያበቃ ጥምቀት
አጠምቃችኋለሁ ለሱ ተአም
ኖ ኃጣውእ በሚያበቃ ተአም
ኖ ኃጣውእ አስተምራችኋለ
ሁ እንጂ ክርስቶስ አይደለ
ሁም።
ወዘይመጽእ እምድኅሬየ ወ-እ
ቱ ይጸንዕ እምኔየ።
ከኔ በኋላ የሚመጣው እሱ
ከኔ አስቀድሞ የነበረው ነው
አለ። የባሕርይ አምላክ ነው።
ዘኢይደልወኒ እፁር ዓዝዕና።
ጫማውን ልይዝ የማይገባኝ።
ሐተታ የንጉሥን የንጣሥትን
ጫማ ትበቃለህ ያላሉት ሰው
አይዝምና። አንድም ባሕርዩን
ልመረምር ከማይቻለኝ። አን
ድም። እሱ ከሚያደርገው ከታ
ምራቱ ከትሩፋቱ አንዱን ላ
ደርግ ከማይቻለኝ። አንድም
አግዕነ መርገምን ከምዕመናን
ለአንዱ አርቅለት ዘንድ ከማ
ይቻለኝ ከኔ አስቀድሞ የነበ
ረ ነው።
ውእቱሰ ያጠምቀክሙ በመን
ፈስ ቅዱስ ወበእሳት።
እሱ ግን በጀ ብትሉ በመን
ፈስ ቅዱስ በጀ ባትሉ በገሃ
ነመ እሳት ያጠምቃችኋል። ገ
ሃነምሰ ምድር ይእቲ እንተ
ኢትመልዕ ማየ አንዲል። ፩ም
በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያ
ጠምቃችኋል። ሐተታ መንፈስ
ቅዱስን እሳት አለው፣ እሳት ም
ሉዕ ነው። መንፈስ ቅዱስም ም
ሉዕ ነውና፣ እሳት በምልዓት ሳለ
ቡላድ ከልመቱ አይገለጽም።
መንፈስ ቅዱስም ቋንቋ ሲያ
ናግር ምሥጢር ሲያስተረጉ
ም እንጅ አድሮ ሳለ አይ
ታወቅምና፣ እሳት ከቡላዱ ሲ
ወጣ በመጠን ነው ኋላ በእ
ንጨት እያቀጣጠሉ ያሰፋታ
ል መንፈስ ቅዱስም በጥም
ቀት ሲሰጥ በመጠን ነው። ኋ
ላ በሥራ ያሰፋታልና እሳት
ጣዕምን መዓዛን ያመጸል። መ
ንፈስ ቅዱስም ጣዕመ ጸጋን
መዓዛ ጸጋን ያመጣልና። እሳት
በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይ
ሆናል። ከመጠን ወጥቶ የሞቁ
ት እንደሆነ ግን ያቃጥላል።
መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በ
ተጻፈው የመረመሩት እንደሆ
ነ ሕይወት ይሆናል፤ በማይገባ
ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩ
ት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና፣
እሳት በላሚ ለዓማፅያን ለእለ
ይክህዱ ስሞ ወእሳት ማሕየ
ዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ
ፈቃዶ እንዲል፣ እሳት ያቀረቡ
ለትን ሁሉ ያቃጥላል መንፈስ
ቅዱስም ሕዝብ አሕዛብ የጸ
ለዩትን ጸሎት ያቀረቡትን መ
ሥዋት ይቀበላልና፣ እሳት ው
ሀ ገደል ከልከለከለው ሁሉን

የማቴዎስ ወንጌል ።

ላጥፋ ቢል ይቻለዋል።መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ከልክለከለው ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋልና እሳት ዱር ይገልጻል መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጻልና እሳት የበላው መሬት ለእህል ለተክል ይመቻል ፣ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ሰውነት ለገድል ለትሩፋት ይመቻልና እሳት ከዛጎላቸው ሳይሰተፍ ሰባቱን መዓድናት ያጸራቸዋል መንፈስ ቅዱስም ከግብራቸው ሳይሰተፍ ሁሉን ያነጻልና ይእቲ ታነጽሕ ወኢት ረስሕ እንዲል።እሳት ከንዱፋና አምሳ ስልሳ ፋና ቢያበሩለት ተከፍሎ የለበትም።መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖር በት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ይኖራልና ይእቲ ትሁብ ወኢትቀብል እንዲል በእሳት ቀድሞ ሰብአ ሰዶም ሰብአ ገሞራን ከእስራኤል አንዱን ጎብር አጥፍቶበታል ለመዓት እንጅ ለምሕረት አልተፈጠረም እንዳይሉ ለምሕረትም እንደ ተፈጠረ ለማጠየቅ ።አንድም ሽክላ ሠሪ ሠርታ ስትጨርስ ነቅ ያገኘችበት እንደሆነ እንደገና መልሳ ከስክሳ በውሀ ለውሳ በእሳት ታድሰዋለች።ተሐድሶም በመንፈስ ቅዱስ ነውና።ዛቲ እሳት እንተ ከነ ይትዓፀፋ አዳም እንበለ ይትዓደ ትእዛዘ እግዚአብሔር ፈጣሪሁ አመ ነበረ ውስተ ገነት ወሶበ በልዓ እምዕፀ ዕልወት ተዓርቀ ወኢረከባ እስከነ መጽአ አዳም ጸግሟዊ ወአልበሶ እመ እግደ ወእመንፈስ እንዲል

፲፱ ዘመሥኤ ውስተ እደሁ ዘበቱ ያነጽሕ ዓውደ አክሉ ።

፲፱ ፍሬውን ከገለባ የሚለይበት መንሽ በጁ ተይዞ ያለ።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ።

ፍሬውን ከገለባው ለይቶ በሪቅ በጎታ በጎተራ የሚሰበሰብበት ወንሠርሶ ያውሳ በእሳት ዘኢይጠፍዕ። ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት የሚያቃጥል እሱ ያጠምቀክሙ በል ወደ ወርቅ ሂዶ ዘኢይጠፍዕ አለ።አንድም ዘመሥኤ ብለህ መልስ።ጣቱ ሰስት ነው በሉ የሰስትነት መያዣው ያንድነት ሁለት ነው በሉ ንዑና ሑሩ የሚልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን።

ዘበቱ ያነጽሕ ዓውደ አክሉ ዘውእቱ ፍጥረተ ሰብእ ብሎ ወስዶታል ሊቁ።ጻድቃንን ከኃጥአን የሚለይበት።

ወያስተጋብእ ሥርናዮ ውስተ መዛግብቲሁ።ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ በመንግሥተ ሰማያት የሚያኖርበት። መዛግብት ብሎ አበዛ በብዙ ወገን ትወረሳለችና።እስመ ውስተ ቤተ አቡየ ብዙኅ ማኅደር ወምዕራፍ ቦቱ እንዲል።

ወንሠርሶ ያውሳ በእሳት ዘኢይጠፍዕ።ኃጥአንን ከጻድቃን ለይቶ በገሃነም ሥቃይ የሚያመጣበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን።አንድም ክፉውን ሕሊና ከበጎው ሕሊና የሚለይበት ሥልጣን ከህነት ገንዘቡ የሚሆን።ወሥርናዮሰ በጎውን ሕሊና ከክፉ ሕሊና ለይቶ በመንፈስ ቅዱስ የሚያስጠብቅበት እሱ።መዛግብት ብሎ አበዛ ስለ ሀብቱ ብዛት ወንሠሮሰ።ክፉውን ሕሊና ከበጎ ሕሊና ለይቶ በቀኖና የሚያጠፋበት ሥልጣነ ክህነት ገንዘቡ የሚሆን እሱ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል

በእንተ ጥምቀተ እግዚእ ኢየሱስ

፲፫ ወአሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምገሊላ ውስተ ዮርዳኖስ ከመ ይጠመቅ እምዮሐንስ ማር

፲፫ ፩ ፲፫ ለጌታ ሠላሳ ሲመላው ለዮሐንስ መንፈቅ ሲተርፈው ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ።አንድም ሰው ሰብስቦ በማያጠምቅበት ጊዜ መጣ።አብ በደመና ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመጥ አንድነት ሰስትነት ይታወቃልና ። ያን ጊዜ ጌታ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ አለ።ሐተታ ምነው ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጅ ጌታ ወደ ባሪያ ይሄዳልን።ባሪያ በጌታው እጅ ይጠመቃል እንጅ ጌታ በባሪያው እጅ ይጠመቃልን ቢሉ ጌታ መምጣቱ ለትሕትና ነው እንጅ ለልዕልና አይደለምና ፣ አንድም ለአብነትነት ጌታ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ብሎት ቢሆን ዛሬ ነገሥታት መኳንንት መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበርና ።ሂዳችሁ ተጠመቁ

ወንጌል ዘማቴዎስ ።

ልግለት አብነት ለመሆን ።ጥም ቱን በዮርዳኖስ ያደረገው ስለ ምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ለ ፈጸም ።ትንቢት በሕርኒ ርእየት ወነየት ወዮርዳኖስኒ ገብዓ ድኅ ሬሁ ርእዩከ ማያት አግዚአ ርእ ዩከ ማያት ወፈርሁ ተብሎ ተነ ግሯል።ምሳሌም ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ ነው ዝቅ ብሎ በደ ልት ይከፈላል ከታች ወርዶ ይ ጠናኛል።ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አን ድ እንደሆነ የሰው ሁሉ ነቁ አንድ አጸም ነው ። ዝቅ ብሎ ወደልት እንዳከፈል እስራኤል ፀግዘረት አሕዛብ በቀኍልፈት ተለያይተዋል ። ከታች ወርዶ ፀመደብ እንዲገናኝ ሕዝብና እሕዛብ በክርስቶስ በጥምቀት አንድ ሁነዋልና ።አንድም አብ ርሃም ላምስቱ ነገሥት ሰዶም ረድቶ አራቱን ነገሥት ከሎ ዶንሞርን ድል ነሥቶ ሲመለ ስ ደስ ቢለው በመዋዕልየነ ትረኑ ታለከ ወሚመ ታርእ የኒሁ ኪያሃ ዕለተ አው አልበ አለ ፡ እሱንስ አታየውም ምሳ ሌውን ታያለህና ሑር ዕድም ለዝንቱ ዮርዳኖስ ፡ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ አለው ፡ ዮርዳ ኖስን ተሻግሮ ፀሂድ መልከ ጼዴቅ ጎብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት ይዞ ተቀብሎታል አ ብርሃም የምዕመናን ዮርዳኖስ የጥምቀት መልከ ጼዴቅ የቀ ሳውስት ጎብስተ በረከት ጽዋ ዓ አኰቴት የሥጋው የደሙ እንደም ኢዮብ ከዚህ ተጠ ምቆ ከደዌው ድኑዋል ፤ ኢዮብ የአጸም ከነሕፃናቱ ደዌ የመ ርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ፤ አ ንድም እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብ ተዋል ፡ ምዕመናንም እምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ገብተዋልና ።ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ገነት አር ጓል ምዕመናንም እምነው ተ ጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰ ማያት ለመግባታቸው ። አንድ ም የኤልሳዕ ደቀ መዛሙርት ጸበበነ ማኅደር ንው ንግዝም ዕፀ ወንሕንፅ ከልን ማኅደረ ብለው ሄዱ።እሱም መምሕረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቄ ርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባሕር ገባበት ፡ ዝኒ ኅቡይ እ ግዚእየ ፡ ጌታዬ ጥንቱን የተ ውሰ ያውም ጠፋ ተጨርሶ አለው የገባበትን አሳየኝ አለ ው አሳየው ቅርፍተ ዕፅ ቀርፎ አመሳቅሎ ቢመታው መዝቀጥ የማይቻለው ቅርፍተ ዕፅ ዘቅ ጠ መዝቀጥ የሚገባውን ብረ ት ይዘት ወጥቷል እንደዚህ ም ሁሉ ሞት የማይገባው መ ለከት ሙቶ ሞት የሚገባው አጸምን ለማጸኑ ምሳሌ ፡ ጥም ቀቱንም ሽቶ አላደረገውም። አከ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመ የሀበነ ሱታፌ ንጽሕ እንዲል በመጠመቁም ጸጋ ያገኘበት አይደለም ። አከ ዘረከበ ጸጋ በ ተጠምቆቱ አላ ከመ ያብርህ መክኖተ ወያጎይል ማያተ ለእ ለ ሀለምሙ ይጠመቁ ውስቴ ታ እንዲል ፡ ዮርዳኖስን ብርህ ት ማሕፀን ለማድረግ ለጥም ቀት ኃይል ለመስጠት ነው እ ንጂ ። አንድም ዮርዳኖስ በበጋ የማይጐድል በክረምት የማይ ተርፍ ማዕከላዊ ውሀ ነው የጌ ታም ጥምቀቱ እኛም ከመጥቀ ም በላይ እሱን ከመጥቀም በ ታች ነውና ።ዳግመኛ በባሕረ ጥብርያዶስ ላይ የሚሄድ ውሀ ነው ወባይ በጣና ላይ እንዲሄድ የጌታም ጥምቀት ከኛ ጥምቀ ት በላይ ነውና ።አንድም ብዙ ንውሰን አንትዕፅ ይገቡበታል እሱ ያበረታቸዋል እንጂ እነ ሱ አያበረቱትም ፤ የጌታም ጥ ምቀት ለኛ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ ይሆናል እንጂ የኛ ጥ ምቀት ለጌታ ጥምቀት ኃይል ጽንዕ አይሆንምና ።አንድም ን ዕማን ከዚህ ተጠምቆ ከደዌ ው ተፈውሷል ንዕማን የአጸ ም ከነሕፃናቱ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ ዮርዳኖ ስ የጥምቀት ምሳሌ ።ኢዮብ ን ዕማን ጌታ የተጠመቁበት ወደ ቡ አንድ ነው ።ትንቢቱን አ ውቆ አናግሯል ምሳሌውንም እንጂ አውቆ አስመስሏል ።ም ሥጢሩ እንደምነው ቢሉ ዲ ያብሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋ ርዶ በአጸምና በሔዋን ሥቃይ አጸናባቸው ስመ ግብርናታች ሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ ባቀ ለልሁላችሁ ነበር አላቸው ።አ ጸም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ብለው ጽ ፈው ሰጡት ፡ መጻፉስ የለም ይሁንብን ማለታቸውን መናገ ር ነው እንጂ እሱ በሁለት ፅ ጠነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮ ርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎ ታል ፡ በዮርዳኖስ የጣለውን ሲ

ጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረግ
ጠ እንደ አምላክነቱ አቅልጠ
አጥፍቶላቸዋል ። በሲኦል የጣ
ለውን በዕለተ ዓርብ በአከለ
ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወ
ጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል ።
፲፱ ወዮሐንስስ ዓበዮ እንዘ ይብል
አንሰ አፈቅድ እምኀቤከ እጠ
መቅ ።
፲፱ ዮሐንስ ግን ባሪያ በጌታው
እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በ
ባሪያው እጅ ይጠመቃልን ብሎ
አይሆንም አለው ።
ወአኀተኑ ትመጽእ ኀቤየ ።
ባሪያ ወደ ጌታው ይሄዳል እ
ንጂ ጌታ ወደ ባሪያው ይሄዳ
ልን አለው ፤ እናቴ ምንትኑ አነ
ከመ ትምጽኢ ኀቤየ አመ
ለእግዚእየ ብላ ነበርና ። ከዚ
ያ አያይዘ እንዲህ አለ ።
፲፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ
ወይቤሎ ኀድግ ምዕረሰ ።
፲፭ ጌታ መለሰ አንድ ጊዜስ ተው
አለው ። ሐተታ እንድ ጊዜ ቢ
ጠመቅ ሁለተኛ ፤ በፈቃድ ቢ
ጠመቅ በግድ ፤ በሰውነቱ ቢጠ
መቅ ባምላክነቱ መጠመቅ የለ
በትምና ።
እስመ ከመዝ ተድላ ውእቱ ለነ
ይህ ለኛ ተድላችን ነውና ።
ሐተታ ። ራሱን ከዮሐንስ አግ
ብቶ አንተም መጥምቀ መለ
ኮት ተብለህ ክብርህ ይነገራልና
እኔም በባሪያው እጅ ተጠመ
ቀ ተብሎ ትሕትናዬ ይነገራልና
ወይደልወነ ከመ ንፈጽም ኵሎ
ጽድቀ ።
ትንቢተ ነቢያትን ልንፈጽም
ይገባናልና ዮሐንስ እንዲያጠ
ምቅ ጌታ እንዲጠመቅ ትን
ቢት ተነግሯልና ። አንድም እ
ስመ ከመዝ ተድላ ለነ ። ራሱ
ን ከምእመናን አግብቶ ይህ
ለኛ ተድላችን ነውና ። አናን
ተም ብትጠመቁ ይወርድላ
ችኋል ለማለት ። ወይደልወነ ከ
መ ንፈጽም ኵሉ ጽድቀ ።
ጽድቀ ተሰብአን ልንፈጽም ይ
ገባናልና ። አንድም ራሱን ከአ
ብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አን
ድ አድርጎ ይህ ለኛ ተድላች
ን ነውና ፩ለ ። አብ ዝንቱ ው
እቱ ወልድየ ብሎ ሲመሰክር
መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግ
ብ ወርዶ ከራሱ ላይ ሲቀመ
ጥ አንድነት ሶስትነት ይገለጻ
ልና ። ወይደልወነ ከመ ንፈጽም
ኵሉጽድቀ ። በማኅፀን የጀ
መርነውን ቸርነት ልንፈጽም
ይገባናልና ።
ወእምዝ ኀደጎ ።
ከዚህ በኋላ ተወው ። ሐተታ ፤
እንዲያው አይተወውም ስመ
አብ ብክ ወሰመ ወልድ ለሊ
ክ ወስመ መንፈስ ቅዱስ ህል
ው ውስቴትክ ባዕደ አጠምቅ
በስምክ ወበስመ መኑ አጠ
ምቅ ኪያክ አለው ። ወልዱ ለቡ
ሩክ ከሣቴ ብርሃን ተሣሃለነ ፤
አንተ ከህኑ ለዓለም በከመ
ሚመቱ ለመልክ ጼዴቅ ብለህ
አጥምቀኝ አለው ። ከዚህ በኋላ
ተያይዘው ወደ ባሕር ወር
ደዋል ።
፲፮ ወተጠሚቆ እግዚእ ኢየሱስ
ሶቤሃ ወፅአ እማይ ። ሉቃ ፫ ፣
ግዕ፩ ፣ ግሩ ፣
፲፯ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ
ተጠመቀ በኋላ ከውሃው ወጣ
ሐተታ ። ጥምቀቱን በውሀ ያደ
ረገው በሌላ ያላደረገው ስለ
ምን ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው
ሊፈጸም ። ትንቢት መእነገ፡ኑከ
ሙ በግይ ንጹሕ ወትነጽሑ
እምርኩስክሙ ተብሎ ተነግ
ሯል ። ምሳሌም ለታውፅእ ባሕ
ር ኵሉ ዘይትሐመስ ዘበ መን
ፈሰ ሕይወት ባለ ጊዜ በልብ
የሚሳቡ በእግር የሚያሽከረ
ክሩ በክንፍ የሚበሩ በደመ
ነፍስ ሕያዋን ሁነው የሚኖሩ
ፍጥረታት ተገኝተዋል ። በረው
በረው የሄዱ አሉ ከዚያውም
የቀሩ አሉ ። በረው የሄዱ የኢ
ጦጭቃን ከዚያው የቀሩ የጥ
ጭቃን ምሳሌ ። ይህስ እንዳይ
ሆን ወበረከሙ ለክልኤሆሙ
በአሐቲ በረከት ይላል ብሎ
በልብ የሚሳቡ የሰብአ ዓለም
በእግር የሚያሽከረክሩ ከትሩ
ፋት ወደ ትሩፋት የሚሉ የበ
ሕታውያን ። በክንፍ የሚበሩ ተ
መስጠ ያላቸው የሰማዕታት
ምሳሌ ትንቢቱን አውቆ አና
ገራል ፤ ምሳሌውንም እንጂ ባ
ወቀ አስመስሏል ፍጻሜው እ
ንደምነው ቢሉ ውሀ በዙፋን
ከለ ንጉሥ ባደባባይ እስ
ከለ ጽጉስ ለሁሉ ርኩብ ነው
ጥምቀት መሠራቱ ለሁሉ ነ
ውና ። ውሀ ጽንፍ እስከ ጽንፍ
ይፈሳል ። ጥምቀትም ጽንፍ እ
ስከ ጽንፍ ይደረጋልና ። ውሀ
ያነጻል ጥምቀትም ያነጻልና ።
ውሀ ለወሰደው ፍለጋ የለው
ም ። በጥምቀትም የተሰረየ ኃ
ጢአት ዳግማ አይመረመርም
ና ። ውሀ መልክ ያሳያል መ
ልክ ያለመለግል ። ጥምቀትም
መልክአ ነፍስ ያሳያልና መል

ክአ ነፍስ ያለመልማልና።በው
ሀ የታጠበ ልብስ ኃይል ጽን
ፅ ግዘፍ እየነሣ ይሄዳል ም
ፅመንናም ተጠምቀው ገድል
ትሩፋት እያከሉ ይሄዳሉና።አ
ንድም ሥጋዊ ተፍነሮ የነር
ብቃ የነሲፓራ በውሀ ምክን
ያት ሁኑዋል መንፈሳዊ ተፍ
ጎርንም በውሀ ለማድረግ።አ
ንድም ሸክላ ሠሪ ሠርታ ስት
ጨርስ የነቃባት እንደሆነ እን
ደገና ከስክሳ በውሀ ለውሳ ታ
ድሰዋለች።ተሐድሶም በጥምቀ
ት ነውና፡አንድም በውሃ ቀ
ድሞ ሰብአ ትክትን ኋላ ግብ
ፃውያንን ከጠፋብት በኋላ ለ
መግት እንጂ ለምሕረት አል
ተፈጠረም ብለው ታል፡ለምሕ
ረትም እንደተፈጠረ ለማጠየ
ቅ።ሐተታ የወዲያኛው ቀስቱ
ን እያጋለ መርዝ እየቀባ እያ
ተባ ያመጣል።የወዲህኛውም
እግዚአብሔር ጥበቡን ገልጸ
ለት ጀባውን ከውሀ ነክሮ ለ
ጋሻው አልብሶ ይሄዳል መር
ዙን ጀባው ይጠርግለታል፡ግ
ለቱን ውሀው ያቀዘቅዝለታል
ስለቱን ጋሻው ይመልስለታል
እንደዚህ ሁሉ ምዕመናንም
በጥምቀት ባገኙት ኃይል ድ
ል ይነሳሉና።

ወናሁ ተርጎመ ሎቱ ሰማያ።
ሰማያ ተከፈተለት ። ሐተታ ።
በሰማያ መከፈት መዘጋት የለ
በትም ያ፫ በተከፈተ ጊዜ የው
ስጡ እንዲታያ ያልተገለጸ ም
ሥጢር ተገለጸለት ሲል ነው።
ወርአየ መንፈሰ እግዚአብ
ሔር እንዘ ይወርድ ከመ ር
ግብ ወነበረ ላዕሌሁ።

መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግ
ብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመ
ጥበት አየ ። ሐተታ ፡መንፈስ
ቅዱስን ርግብ አለው ርግብ
ኃዳጊተ በቀል ናት።መንፈስ
ቅዱስም ኃዳጌ በቀል ነውና
አንድም ርግብ በኖኅ ጊዜ ሐፀ
ማየ አይኅ ነትገ ማየ አይኅ
ስትል ቄፅለ ዕፀ ዘይት ይዛ
ተገኝታለች ፤መንፈስ ቅዱስም
ተስፋ መስቀልን ያበስራልና።
አንድም ርግብ ክንፏን ቢመ
ታት ዕንቁላሏን ቢሰብሩባት
ቤቷን ካላፈረሱባት አትሄድ
ም።መንፈስ ቅዱስም ኃጠአ
ት ቢሠሩ ፈጽመው ከልክዱት
አይለይምና ። ታሪክ ፡አንድ ባ
ሕታዊ እንጻየው ወለተ ከህነ
ግልፎን አጊጣ አይቶ በሐፀ ዝ
መት ተነደፈ ። ላግባሽ አላት
ላበቱ ንገረው እምቢ አይል
ሀም አለችው ሂዶ ነገረው ።
ፈጣሪዬን ልጠይቅ ብሎ ከጣ
ያቱ ዘንድ ገብቶ ልስጠው
አልስጠው ብሎ ጠየቀው።ቆ
ቡን ይቅደድ ፈጣሪውን ይክድ
ይሽን ካላደረገ አትስጠው አ
ለው ሂዶ ነገረው።ቆቡን ቀደ
ደ ፈጣሪውን ካደ ። በዚህ ጊዜ
አድሮበት የነበረ መንፈስ ቅ
ዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ተ
ለይቶት ሲሄድ አይቷል ።ያል
ኸኘን አደረግሁ ስጠኝ አለው
ሁለተኛ ልጠይቅ ብሎ ገብ
ቶ ቢጠይቀው ። ቄይ ፈጣሪ
ውም ፈጽሞ አልራቀውም
ባጠገብ ባጠገቡ ይጠብቀ
ዋልና አትስጠው አለው ።
አይሆንም አለው፡ለዚህን ብ
ዬ ፈጣሪዬን ከድሁ ቆቤን ቀ
ደድሁ ብሎ ንስሐ ቢገባ ተ
መልሶ በርግብ አምሳል ሲያ
ድርበት አይቷል ። ጥምቀቱን
በመዓልት ያላደረገው በሌሊ
ት ያደረገው ስለምን ቢሉ ።
በመዓልት አድርጎት ቢሆን
መንፈስ ቅዱስን በቁሙ ርግ
ብ ነው ብለው በተጠራጠሩ
ነበርና ።አሁንስ በቁሙ ርግብ
አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ
መሆኑ በምን ይታወቃል ቢ
ሉ ።ጌታ የተጠመቀ ከሌሊቱ
ባሥረኛው ሰዓት ነው በዚያን
ጊዜ ተሐዋስያን ከየቦታቸው
እይናወጡምና ። በቁሙ ርግብ
አለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ መ
ሆኑ በዚህ ይታወቃል፡መንፈ
ስ ቅዱስም መውረዱ ከውሀ
ው ከወጣ ከዮሐንስ ከተለየ
ነው ።ከወሀው ሳለ ወርዶ ቢ
ሆን ለቀድሶተ ማያት የወረደ
ነው ባሉ ነበረና ከዮሐንስ ጋ
ራም ሳለ ቢሆን ስለ ከብረ
ዮሐንስ የወረደ ነው ባሉ ነበ
ርና ።ረቦ ወርዷል ያሉ እንደ
ሆነ አብ ምሉዕ ነው እንተም
ምሉዕ ነህ እኔም ምሉዕ ነኝ ሲ
ል ።አሰይፎ ወርዷል ያሉ እን
ደሆነ የብሉየ መዋዕል የአብ
ሕይወት ነኝ የብሉየ መዋዕል
ያንተም ሕይወት ነኝ እኔም ብ
ሉየ መዋዕል ሕይወት ነኝ ሲ
ል ወርዶ ራሱን ቄንጠጥ አድ
ርጎ ይዘታል አብ አኃዜ ዓለ
ም ነው አንተም አኃዜ ዓለም
ነህ እኔም አኃዜ ዓለም ነኝ ሲ
ል ።መውረዱ ግን የማጎፅኑን
ለመግለጽ ነው ።አንድም ለአ
ብነት እናንተም ብትጠመቁ እ
ንዲህ ይወርድላችኋል ለማለት

ወናሁ መጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘእፈቅር ዘበቱ ሠመርኩ ። ሉቃ ፱ ፴፭ ። ፲፯ ለተዋህዶ የመረጥሁት በሱ ሀልው ሁኜ ልመለክበት የወደድሁት ልጄ ይህ ነው የሚል ቃል ከወደ ሰማይ ተሰማ ሐተታ ። በዚህ አድሮ ያለው ልጄ ነው አላለም ፩ድ አከል ፩ በሕርይ አድርጎ ይህ ልጄ ነው አለ እንጂ ።ኢይቤ ዘላዕለ ዝንቱ ወልድየ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ እንዲል ።ወልድየም ግለቱ እንደ አምላክነቱ ነው እንጂ እንደ ሰውነቱ አይደለም ። ኢይቤ ዝንቱ ወልድየ ዘከመ ትስብእቱ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘከመ መለኮቱ እንዲል ።

በእንተ ተመክሮት ዘኢየሱስ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ ለእግዚእ ኢየሱስ ።ማር ፩ ፩ ፲፪ ሉቃ ፬ ፩ ከተጠመቀ በኋላ ፈቃዱ አነሣስቶ ወደ ገዳም ወሰደው ። ወሰበ ትሰምዕ እንዘ ይብለከ መንፈስ ወሰዶ ገዳመ ኢተሐሊኬ ከመ ፍጡር ውእቱ ። አላ መንፈስሰ ሥምረቱ ይእቲ እንዲል ።አንድም መንፈስ ቅዱስ የሚል አብነት ይገኛል ሰማዕታትን አነሣስቶ ወደ ደም ጻድቃንን አነሣስቶ ወደ ገዳም እንዲወስድ ወሰደው ማለት አይደለም ፈቃዳቸው አንድ መሆኑን መናገር ነው ።ተጠምቆም አልዋለም አላደረም ዕለቱን ገዳም ሂዷል ።እናንተም ተጠምቃችሁ እትዋሉ እትደሩ ዕለቱን ገዳም ሂዳ ለማለት አብነት ለመሆን ወደ ገዳም ሄደ አለ ። አዳም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገነት ድል ተነሥቶ ነበርና ። እሱም ከዚህ ዓለም አፍአ በምትሆን በገዳም በቮቱ አርእስተ ኃጣውእ ድል ለመንሳት ። አንድም በገዳም ያር ይቀላል ለወጣንያን አብነት ለመሆን አንድም በገዳም ያር ይጸናል ለፍጹማን አብነት ለመሆን ።

ከመ ይትመከር እምዲያብሎስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ፣ እፈተናለሁስ ብሎ ሄዶ ቢሆን ዕዳ በሆነበት ነበር ።ከሄደ ዘንድ ያሩን እየቀለመ ይሰብርበታል እንጂ ።

ይህንም ያር እግርበታለሁ ብሎ አላደረገውም ንግእ ፩ድ መሻዴ እምአፍአ ከመ ትኩን ፍቱነ ወስቡከ እንዲል መ ከራውንም ሽቶ አላመጣውም አከ ፈቂዶ መከራው ለጸላኢ አላ ከመ ያብጥል ኃይሎ ለዘ ያሜክር በኃይሉ ለቃል ዘከነ ፩ደ ምስለ ሥጋ እንዲል ።መ ከራውንም አነሣስቶ አለመጣውም ኢሆከ አግዚእነ እሱ ንተ ሕማማተ ከመ ይኅልፉ ዲቤሁ አላ በሁከቶሙ ማሰኑ እንዲል ።መዋጋቱም በሰውነቱ ነው ፣ኢሠርዓ እግዚእነ ቀትለ በመለከቱ አላ በሥጋሁ ዘይ ትዌከፍ ሕማማተ እንዲል ። ድል መንሳቱም በሰውነቱ ነው እንጂ በአምላክነቱ አይደለም ወኢሞየ በኃይሉ መዋጊት እንዲል ።በአምላክነቱስ ድል ቢነሳው ባልተደነቀም ነበር ፣ሰበሰ ሞየ እግዚእነ በኃይሉ መዋጊት እምኢከነ መንክረ ወእምኢከነት ትሩፋት ዘውስቴቱ ዘኢስብሕት ወዘኢውድስት አኮ መንክር እመ ሞየ ኃያል ለድኩም እንዲል ።

፪ ወጸመ ፵ መዓልተ ወ፵ሌሊተ ፪ ፵መዓልት ፵ሌሊት ጸመ ።ሠራዔ ሕግ ነውና ጸምን መጀመሪያ ሕግ አደረገ ። አንድም ሥራውን በጸም ጀመረ ።ሐተታ መብል ለኃጣውእ መሠረት እንደ ሆነ ፣ጸምም ለምግባር ለትሩፋት መሠረት ናትና ።እግለጸሎት ወእጎታ ለአርምሞ ወነቅዓ ለአንብዕ ወጥንተ ሁሉ ገድል ሠናይት እንዲል ። ፵መዓልት ፵ሌሊት መሆኑ ስለምን ቢሉ ቀድሞ አብቶቹ ነቢያት ፵፵ጹመዋል ከዚያ በኋያተርፍ አተረፈ በያጕድል አጕደለ ብለው አይሁድ ደግቱን ሕገ ወንጌልን ከመቀበል በተከለከሉ ነበረና ፣ሙሴ በ፵ዘመኑ ለዕብራዊ ረድቶ ግብፃዊን ገድሎ በናፃ ቀብሮ ታል ።ሙሴ የወልደ እግዚአብሔር ዕብራዊ የአዳም ግብፃዊ የዲያብሎስ ኖፃ የመስቀል ። አንድም የቮቱ አርእስተ ኃጣውእ ምሳሌ ።ሙሴ ፵ጹሞ ሕገ ኦሪትን ሠርቷል እሱም ፵ጹሞ ሕገ ወንጌልን የሚሠራ ነውና ሙሴ፵ዘመን በምድያም ኦሮ አስራኤልን ከግብፅ አውጥቷቸዋል ።እሱም ፵ጹሞ

ወንጌል ዘማቴዎስ።

ነፍሳትን የሚያወጣ ነውና ። አንድም የእስራኤል ገብኞች በሃቀን ተመልሰዋል። እሱም የመንግሥተ ሰማይ ገብኖ ነውና እስራኤል በገዳም ሃዘመን ኑረው ምድረ ርስት ገብ ተዋል። እናንተም ሃብትጸመንነት መንግሥተ ሰማያት ት ገባላችሁ ለማለት። ኤልያስ ሃጸሞ ገነት ገብቷል። እናንተም ሃብትጸመ ገነት መንግሥተ ሰማያት ትገባላችሁ ለማለት። ሕዝቅኤል በፀጋማይ ጐኑ ሃቀን ተኝቶ ስድስት መቶ መታን አስነሥቷል ። እናንተም ሃብትጸመ ትንሣኤ ዘለክብር ትነሣላችሁ ለማለት ። ዕዝራሃቀን ከምግቡ ተከልክሎ መጻሕፍትን አጽፏል። አንሰ በውአቶን መዋዕል ኢበላዕኩ እክለ ወኢሰተይኩ ማየ። እመንቱሰ መዓልተ ይጽሕፉ ወሠርከ ይደረሩ እንዳል እነዚያ ቀን ሲጽፉ እየዋሉ ማታ ይ መገባሉ ። እሱ ግን ቀን ሲያጽፈው የሚውለውን ሌሊት ሲያስበው ይድር ነበር ። እናንተም ሃብትጸመ ምሥጢር ይገለጥላችኋል ለማለት ። እባብ አክሉ የደገደገበት እንደሆነ ሃቀን ከምግብ ተከልክሎ ይሰነብታል ። በስቀረተ ዕፅ በስቀረተ ዕብንም ቢሉ አልፎ ሲሄድ ተገፎ ይወድቅለታል ይታደሳል።እናንተም አርባ ብ ትጸመ ተሐድሶተ ነፍስ ታገኛላችሁ ለማለት ። ምሳሌውን አውቆ አስመስሏል ፍጻሜው እንደምን ነው ቢሉ አዳም በ ሃቀን ያገኘውን ልጅነት አስ ወስዶ ነበርና ለሱ እንደከሰ ለ ማጠየቅ ። አንድም በሃቀን ተ ስእሎተ መልክዕ ለተፈጸመለ ት ሰው ሁሉ ሊከስ እንደመ ጣ ለማጠየቅ።ላይቱ ባሕርያ ት አሥር አሥሩን ለመከስ። አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን የ ጨመሩ እንደሆነ ስምንት ስምንቱን ሊከስ እንደመጣ ለማጠየቅ ። ከዚህም ተራበ አልሳሳም ተዋጋ ድል አል ተነሣም ወሰበ ጸመ እግዚእ ሃመዓልተ ወሃሌሊተ ከሠተ ከመ ኢሐመ ሥጋሁ እምረኃ ብ ወፅምዕ በኃያል ዘይደሉ ለመለኮት እንዲል ። ከዚህም ሥራውን ሠርቶ ሥሩ አለ እ ንጂ ። በልዋጁበት ጣት የዘንዶ ጉድንድ ይለኩበት እንዲሉ ሳይሠራ እኛን ሥሩ አላለንም ወሐሮን እግዚእ ለዕስ ግብ ራት እንዲል፣ዕስ ግብራት የተ በሉ ጥምቀት።ተአምኖ ኃጣውእ ፣ከዊነ ሰማዕት፣ተባሕትዎ ም ንኩስና።ጥምቀት በዕደ ዮሐን ስ መጠመቅ ተአኖ ኃጣውእ ከተአማንያነ ኃጣውእ ጋራ አ ንድ ሁኖ መቄጠር፣ከዊነ ሰ ማዕት አንሰ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ ውስተ ዓለም ከመ እኩን ሰማዕተ በጽድቅ ብሎ ከጲላጦስ ፊት ቁሞ መመስ ከር ተባሕትዎ ሃቀን ከምግ ብ ተከልክሎ በገዳም መኖር። ምንኩስና በድንግልና መኖር ነው።ረቂቅ ዘእምረቂቅ እንደ ሆነ ለማጠየቅ በጎቱም ድን ግልና ተፀነሰ በጎቱም ድንግል ና ተወለደ ። ዘኢይርኅብ እም ዘኢይርኅብ እንደሆነ ለማጠየ ቅ ሃመዓልት ሃሌሊት ጸመ ዘኢይትገሥሥ እምዘኢይትገ ሠሥ እንደሆነ ለማጠየቅ በባ ሕር ላይ ሄደ ። ብርሃን ዘእም ብርሃን እንደሆነ ለማጠየቅ ብ ርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦ ር ገለጸ፣ሕይወት ዘእምሕይወ ት እንደሆነ ለማጠየቅ ያሬት ቀን ሬሳ አልዓዛርን አነሣ ። ወአምዝ ርኅበ ።

ከዚህ በኋላ ተራበ።ሐተታ ረ ኃቡም የፈቃድ ረኃብ ነው እ ጂ እንደኛ ረኃብ አይደለም እኛ ብንበላው ቀኑጣን ብን ተወው ስልት ቀጠና ይሆን ብናል።ረኃበ እግዚእነሰ አኮ ከ መ ረኃበ ዚአነ አላ ገጸ ረኃ ቡ ፍሉጥ እምኔነ ለነሰ በግብ ር ይመውዓነ ወሎቱሰ በፈቃ ዱ እንዲል ። አንድ ጊዜ ርኅበ አንድ ጊዜ ኢርኅበ ይላል እ ንደምነው ቢሉ ። ከፎት አክል ፩ አክል ከሁለት ባሕርይ ፩ባሕር ይ እንደሆነ ለማጠየቅ ።በእንተ ምንት ርኅበ እግዚእነ ዘእንበለ ጸዕሙ ከመ ያጠይቅ ከመ ውእቱ እም፪ ህላዌያት እንዲል ። መራ ቡም ለአጽድቆተ ትስብእት ለ ካሳ ነው። ወቀርበ ዘያሜክር ። የሚፈታተነው ዲያብሎስ ቀረበ ሐተታ እንዲያው አይቀርበው ም ርኅብኩ የሚል ድምፅ አ ሰምቶት ፍሬ ዕፅ ሲሻ አይቶት መልኩን አጸውልጎ ታይቶት እሱም እንዲያው አይቀርብም በአምሳለ ሠዓሊ በአምሳለ ሐ ራሲ በቀዳዳ ሽልም ትኩስ ዳ ቦ የያዘ መስሎ ሁለት ደንጊ ያ ይዘ ይቀርባል እንዴን ላ

ተ አንዱን ለዚህ ለሚሉ አድርገህ እንብላ እለዋለሁ ደንጊያውን ግ ለው ከግድረግ የያዝኸውን እንጀራም ያለኝ እንደሆነ አላ ምን እበቱን በመብል ምክንያ ት ድኋ እንደነሣሁት እሱን ም ይመብል ምክንያት ድል እ ነሣዋለሁ ብሎ።

ወደዲያቡ እመሰ ወልደ እግዚ አብሔር አንተ በል ከመ አላ አዕሸን ጎብስተ ይኩና።

በዮርዳኖስ ዝንቱ ውእቱ ወል ድየ ብሎ ሊመሰክርለት ሰም ቆ ነበርና የእግዚአብሔርስ ል ጅ ከሆንህ እኒህ ደንጊያዎች ጎብስት ይሁኑ ብለህ እዘዝ አ ለው።ቢያደርገው የሰይጣን ተ አዛዢ ብቡ ዕላ አልበታለሁ ባያ ደርገው ደክሞ አሰንዋለሁ።ቢ ያደርገው ሌላ ያር እሸለታለሁ ባያደርገው ድክሙን አይቼ እቀርባለሁ ብሎ።ደንጊያውን ጎብስት አድርግ ማለቱ ምን ልማድ ይዘ ነው ቢሉ በዮሴ ፍ ልማድ።ዮሴፍን አባቱ የሱ ን ስንቅ ለብቻ አሲዘ ለወንድ ሞችህ ስንታቸውን ሰጥተህ ወንድሞችህን ጠይቀህ ና ብሎ ላከው።ያሉበትን አጥቶ ሲፈ ልግ የሱ ስንቅ አለቀበት ከዚ ያ እንዳይበላ አባቱ ያላዘዘው ነ ው።ረኃብ ጸንቶበት ሳለ መ ልእክ ያባትህን ፈጣሪ ደንጊያ ውን ዳቦ አድርግልኝ ልትለ ውም እለው።ወደእግዚአብሔ ር ቢያመልክ ደንጊያው ዳቦ ሁኖለት ተመግቧልና እንዲህ እሰ።

፬ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ። ጌታም መለሰ።

ወደቤሎ ጽሑፍ ከመ እከ በ ጎብስት ከመ ዘየሐዩ ሰብእ። ዘዳ፣፰ ፫ ሉታ፣፬ ፬።

ሰው የሚድነው በጎብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል።

አላ በሁሉ ቃል ዘይወጽእ እ ምአፋሁ ለእግዚአብሔር።

እግዚአብሔር ዳን ያለው ይ ድናል ሙት ያለው ይሞታል እንጂ።አንድም ሰው የሚድን ገበሬ በጸረበት በጎብስት ብቻ እንዳይደለ ተጽፏል፣እግዚአብ ሔር ምግብ ይሁን ያለውም ምግብ ይሆናል እንጂ፣እስራ ኤል ፵ ዘመን በትርሀ አልወደ ተ ጫማህ አልወለቀ ልብስህ አላለቀ እንዲሉ፣ከውቅያኖስ በ ደመና አይበት ተቋጥር በነ ፋስ ወደልጋዝ ተጭኖ መጠ ድንብላል አህሉ መልኩ በረ ድ መስሉ ወእንዘ የኃድግ ህየ ይላል የውርጭ ገበታ ሲነጸፍ እየዘነመላቸው አርባ ዘመን ተ መግበዋልና።አንደም ሰው የ ሚድን ገበሬ በጸረበት በጋረ በት በእንጀራ ብቻ እንዳይደ ለ ተጽፏል።በዓቂበ ሕግም በ ትምህርትም ነው እንጂ።ሐተ ታ።የሰው ባሕርዩ ባሕርይ እ ንስሳዊ ባሕርይ መልአክዊ ነው ባሕርይ እንስሳዊ ምግብ ሲያ ጣ ይጎዳል፣ባሕርይ መልአክዊ ትምህርት ሲያጣ ይጎዳልና።አ እምር ከመ በአማን ሲያይ ቃለ እግዚአብሔር ሲሲተ ልብ ታ ላቲሁ ለእግዚአብሔር ወአም ጽእ ረኃብ እክል ወጽምዋ ማይ ለብሔር ረኃበሰ እምሰሚዓ ቃለ እግዚአብሔር እንዲል። አንድም ወልደ እግዚአብሔር ስ ከሆንህ ይህ እንደ ድንጊያ ፈዘ ያለ ሰውነትህ ጎብስቶ ሕ ይወት ጎብስተ መድኃኒት ይ ሁን ብለህ እዘዝ ሲያሰኘው ነው።ጌታም ሰው የሚድን በ ዕሩቅ ብእሲ ሥጋ እንዳይደል ተጽፏል።አክላዊ ቃል በተዋ ሕዶው ሥጋ ነው እንጂ አለው

፭ ወእምዝ ነሥአ ወወሰዶ ውስ ተ ቅድስት ሀገር።

፮ ከዚህ በኋላ ወደ ቅድስት ሀ ገር ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው ሐተታ።እሱስ አይመስደውም ፈታዱን አውቆ ስለሄደለት ክ ህናትን ድል ነሥቼበት በማላ ውቅ በገዳም ቢሆን ነው እ ንጂ። ክህናትን ድል በም ነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር ብሏ ል ፈታዱን አይቶ ስለሄደለት ነሥአ ወሰዶ አዕረገ ይላል።

ወጎቀሞ ውስተ ተድባበ ቤተ መቅደስ።

